©ዲ/ን ሚኪ ገ.
አቡነ ሺኖዳ ፫

ከአቡነ ሺኖዳ መንፈሳዊ ገፅ የተቀናበሩ ልዩ ልዩ ፅሑፎች

በዲ/ን ሚኪኤለ ገ/ሰላሴ

ሰኔ 1,2012 ዓ/ም

ክፍል 1

በረከታችው ይደርበን!!

-

የምጽዋት ብዛት የሚመዘነው በሚሰ′ጠው ገንዘብ ቁጥር ሳይኾን ስጦታውን በሚሰጥ የልብ ስፋት ነው። አንዲት ድኻ ሴት ያላትን ጥቂት እንጀራ ምንም ከሌላት ከሌላ ሴት ጋር ተካፍላ የምትበላ ከኾነ፥ ወርቅን በሙዳዬ ምጽዋት ከሚጨምር ባለጸጋ ሰው እጅግ ትበልጣለች። ነገር ግን ምንም እንኳን ይህ እውነት እንደ ኾነ ብዙ ክርስቲያኖች ቢያውቁም፥ ምስጋና የሚሰጡት ወርቅ ለሰጠው ነው።

አንድ ባለጸጋ ጠቀም ያለ ገንዘብ ለቤተ ክርስቲያን ቢሰጥ እጅግ ያመሰግኑታል፤ ካለው የሀብት ብዛት የተነሣ ያንን በመስጠቱ ምንም ባይጎድልበትም እንኳ፥ በሰዎች ዘንድ እጅግ ቸር እንደ ኾነ ተደርጎ ይንቆለጳጳሳል። ድኻው ጥቂት ገንዘብ ቢሰጥ ግን ሰዎች ስለ እርሱ ምንም ትንፍሽ አይሉም። ምናልባት ያቺ የሰጣት ገንዘብኮ በጓላ እርስዋን በማጣቱ ምክንያት ተርቦ እንዲያድር ልታደርገው የምትችል ትኾን ይኾናል፤ ነገር ግን ይህን በማድረጉ የሚያመሰግነው አንድ ሰውስ እንኳ አይገኝም። በእውነት ያለ ሐሰት ምንም ሳይጎድልበት የሰጠውን ባለጸጋውን አመስግኖ ያለውን ኹሉ የሰጠውን ድኻ ሳያመሰግኑ ከሚቀሩ ከእነ ጭራሹ ምስጋና ባይኖር ይሻል ነበር።

ስለዚህ እውነተኛ ምጽዋት የሚባለው የባለጸጋውም ይኹን የድኻው በአግባቡና በሥርዓቱ ልናውቀው ይገባናል። ማመስገን የሚገባንም ከዚያ በኋላ ነው። በሌላ አነጋገር የምስጋናችን ስጦታም ሰዎች ከልባቸው ከሚሰጡት ገንዘብ ብዛት አንጻር ሊኾን ይገባል።

- ቅዱስ ዮሐንስ አፈወርቅ:

ተማሪዎች ፈተና ከመፈተናቸው በፊት ምን ብለው ይጸልዩ?

የግብፅ ቤተክርስቲያን በቅርቡ ማዕረገ ቅድስና የሠጧቸው ቅዱስ አቡነ ቄርሎስ ከሚታወቁባቸው በርካታ በጎ ነገሮች አንዱ ለተማሪዎች የነበራቸው ልዩ ፍቅርና ቅርበት ነበረ። አባ ሚናስ ተብለው ይጠሩ ከነበረበት የምንኩስናቸው ዘመን ጀምሮ አቡኑ በተማሪዎች የተከበቡ ነበሩ። ከልዩ ልዩ ክፍለ ሀገራት ካይሮ ዩኒቨርሲቲ ሊማሩ ለሚመጡ ተማሪዎች የማደሪያ አገልግሎት በቅዱስ ሚናስ ቤተ ክርስቲያን ውስጥ ይሰጡ ነበር። ይህ አገልግሎታቸውም በግብፅ ለዘመናዊው ቤተ ክርስቲያንን የሚያካትት የማደሪያ አገልግሎት(church- affiliated dormitory) መወለድ ምክንያት ሆኗል። የዚህ የማደሪያ አገልግሎት ተጠቃሚዎች የነበሩ ተማሪዎችም ቀሳውስትና ጳጳሳት የቤተ ክርስቲያን መሪዎች ለመሆን በቅተዋል።(ሊቀ ጳጳሱ አቡነ ሳሙኤልና ቅዱስነታቸው አቡነ ሺኖዳ ሣልሳዊተጠቃሽ ናቸው።) በወቅቱ መነኩሴ የነበሩት አባ ሚናስ (አቡነ ቄርሎስ) ለእያንዳንዱ የቤተ ክርስቲያኑ ካህን በተማሪዎቹ መኖሪያ ውስጥ የሥራ ድርሻ ሰጥተው ነበር። የእርሳቸውን የሥራ ድርሻ ምን እንደነበረ ግን ማንም ሰው አላወቀም ነበር። በሌሊት በድብቅ የሚሠሩት ሥራ ካህናቱና በቤተ ክርስቲያኑ የሚኖሩ ተማሪዎች የሚጠቀሙበትን መጸዳጃ ቤት ማጽዳት ነበር።

ይህ ለተማሪዎች ያላቸው በጎ አመለካከት በፓትርያርክነት ዘመናቸው አልተለያቸውም። ተማሪዎች ፈተና ሲደርስባቸው ወደ እርሳቸው እየመጡ ጸልዩልን ይሉአቸው ነበር። አንዳንድ ተማሪዎች ደግሞ የሚያጠኑበትን መጽሐፍ ይዘው መጥተው ያስባርኩ ነበር። ቅዱስ አባ ቄርሎስ አንዳንዴ መጽሐፉን ገለጥ ያደርጉና ‹ይህንን አጥኑ› ብለው ይሠጡ ነበር። የፈተናውም አብዛኛው ጥያቄ ከዚያ ገጽ ይወጣ ነበር። እንዲሁም ለተማሪዎች ፈተና በሚፈተኑበት ጊዜ የሚገጥማቸውን የመንፈስ ጭንቀትና የአእምሮ ውጥረት በመረዳት የሚከተለውን ከፈተና በፊት የሚጸለይ ጸሎት አዘጋጅተውላቸዋል።

<u>+++ ጸሎት +++</u>

‹‹ጌታዬ ኢየሱስ ክርስቶስ

‹‹በችግርህ ቀን ጥራኝ ፤ አድንሃለሁ አንተም ታከብረኛለህ›› ብለህ የአንተን መጠጊያነት መፈለግን ስላስተማርከኝ አመሰግንሃለሁ!

አሁንም ጌታ ሆይ! በዚህ የፈተና ሰዓት ጥበብና ማስተዋልን ትሰጠኝ ዘንድ እማጸንሃለሁ።

ይህን ፈተና በሰላም አልፍ ዘንድ ጸጋን (ሞገስን) ስጠኝ። ፈተናውን በምሠራ ጊዜ ጥልቅ የሆነ ሰላምህንና በረከትህን ስጠኝ።

ጌታዬ ኢየሱስ ውጤት በሚሰጡኝ ጊዜ በመምህራኖቼ ዓይን መወደድን ትሰጠኝና ልባቸውን ታለሰልስልኝ ዘንድ እለምንሃለሁ። የከበርከው ጌታእኔ ኃጢአተኛ ነኝ ፤ ዓመቱን ሙሉ አንተን ደስ አላሰኘሁህም ፤ ውስጤንም ጭምር ፤ ነገር ግን ከልቤ ደንዳናነትና ከኃጢአቶቼ የተነሣ ሳይሆን ከምሕረትህ እና ከርኅርኄህ የተነሣ እንደትረዳኝ እለምንሃለሁ፡

ጌታ ሆይ ‹‹ለምኑ ይሰጣችኋል፣ እሹ ታገኛላችሁ፤ አንኳኩ ይከፈትላችኋል›› ብለሃል። እናም እነሆኝ እየለመንኩ ነው፤ የምሕረትህንም ደጅ እያንኳኳሁ ነው። ‹‹ወደ እኔ የሚመጣውን ከቶ ከእኔ አላወጣውም›› ብለሃልና ጸሎቴን አትናቅ።በቅድስት ድንግልና በመላእክትህ ሁሉ አማላጅነት መልስልኝ!! አሜን!"

ለዘንድሮ ተፈታኝ ተማሪዎች እግዚአብሔር ከእናንተ ጋር ይሁን!

- ዲያቆን_ሄኖክ_ኃይሌ

ገዳማዊ ሕይወት በግብፅ ከተመሰረተበት ጊዜ ጀምሮ በየበረሃው ለሚገኙ አበው ሁለት የመንፈሳዊ ሕይወት መመሪያዎች ነበሯቸው

፩ ቅዱሳት መጻሕፍት

፪ ከቀድሞ አበው የሚገኘው መንፈሳዊ ጥበብ ነው።

ይህ መንፈሳዊ ጥበብ ከኑሯቸዉ የሚገኝ ነበር። በየገዳማቱ ለመንፈሳዊ ተጋድሎ የተሰለፉ የእነዚህን አበው ሕይወትና ንግግር ለማሰባሰብ ብዙ ሊቃውንት በየበረሃው ተጉዘው ነበር።

አባ ሄሮኒመስ ፥ የታሪክ ጸሐፊው ሩፈኖስ ፥ ጳላድያን ፥ ኤቫግሪዮስ እና ዮሐንስ ካስያን ተጠቃሽ ናቸው።

ከገዳማውያን አበው የተገኙት ብሂሎች በተለያዩ ደረጃዎች አልፈው ለዚህ ዘመን መድረሳቸው ይታመናል። የመጀመሪያ ደረጃ እነዚህ መንፈሳውያን አርበኞች አባቶች የሆኑ ገዳማውያን አበው ለሚቀርቡ ለሚጠይቁና በረድእነት ለሚያገለግሉ በየዘመኑ በቃል የተነገሩበት ደረጃ ነው።

ወደ ግብፅና ፍልስጤም በረሃዎች እነዝህን አበው ለማየት በመጡ ክርስቲያኖች አማካኝነት ለ፫፻(300) ዘመናት ቃል በቃል ሲተላለፍ ቆይቷል።

በሁለተኛ ደረጃ ደግሞ እነዚህ በቃል የተላለፉ የአበው ብሂሎች ወደ ጽሑፍ የተሸጋገሩበት ዘመን ነው።ይህም ፬ኛ መ.ክ.ዘ መጨረሻ እና በ፭ኛ መ.ክ.ዘ መጀመሪያ አከባቢ መከናወኑ ይታመናል።

ሦስተኛው ደረጃ ደግሞ የአርትዖት ሥራ ተሠርቶላቸው በተናገሯቸው አበው የፊደል ተራ ቅደም ተከተል ወይም በጉዳያቸው መሠረት የተቀመጠበት ደረጃ ነው። በዚህ መልኩ የተለያዩ ጥራዞች በ፭ መ.ክ.ዘ አጋማሽ መውጣት ጀምረዋል። ከፊደል ቅደም ተከተል በተጨማሪም ጸሎት ትህትና ታዛዥነት ወዘተ በሚሉ ንዑሳን ርዕሶች ተከፋፍለው

ተዘጋጅተው ነበር።

በመካከለኛው ዘመን ወደ ኢትዮጵያ ከመጡ መጻሕፍት መካከል የሚቆጠሩ መጻሕፍተ መነኮሳት (ፈልክሰዮስ በዐፄ ድል ነዐድ አረጋዊ መንፈሳዊ በዐፄ ልብነ ድንግል ማር ይስሐቅ በዐፄ ገላውዴዎስ ዘመን ተተርጉሟል)።

ይዘታቸው ከእነዚህ የአባቶች ብሂል የተቀዳ ነው።

መጽሐፍ መነኮሳትን እየደጋገመ የሚጠቅሰው ጳላድዮስን(palladius) የተባለ ጸሐፊ በግልፅና በፍልስጤም በረሃዎች ተዘዋውረው የእነዚህን አበው ሕይወትና ብሂል ካሰባሰቡት የ፬ኛ መ.ክ.መ ሰዎች አንዱ ነው።

የነዚህን አበው ብሂል ማንበብ በቀደምት የቤተክርስቲያን አባቶች ዘንድ የተለመደ ነው።

አውግስጢኖስ እና ዞሲማስ ብሂሎቹን ያነቧቸው እንደነበር ተዘግቧል። አባ ዞሲማስን በተመለከተ አንድ የታሪክ መዝገብ "ይህ ብፁዕ ዞሲማስ የእነዚህን የተቀደሰ አበው ብሂሎች አዘውትረው ማንበብ ይወድ ነበር። እነርሱ ለእርሱ እንደሚተነፍሰው አየር የሚቆጠሩ ነበሩና። ሁሉንም ዓይነት መንፈሳዊ ሕይወት ፍሬዎችን የለቀሙው ከነዚህ ብሂሎች ነው" ይላል። በልዩ ልዩ ዘጋቢዎች የተሰበሰበው ብሂል ፱፭፮ አበው እና እማት የተናገሯቸውን ፲፱፱፱፱ ብሂሎችን የያዘ ነው። እስቲ ከነዚህ እኛ ስንቱን አንብበናል?

እንግዲህ ያነበብነዉን ለሌሎች እናስተላልፈ።

<u>ብሂለ አበው</u>

"እግዚአብሔር ከፈለግነው ራሱን ይገልጥልናል ፥ አጥብቀን ከያዝነው ከእኛ ጋር አብሮ ይኖራል።"

- **አባ አርሳንዮስ**

"አንድ ሰዉ በእግዚአብሔር ዕቅፍ ውስጥ እንዳለ ካወቀና እግዚአብሔር ሁሉን ያከናዉንልኛል ካለ ልቡ ፍጹም ይሆናል።"

- **ማር ይስሐቅ**

"በቀዳማዊት ሔዋን አለመታዘዝ ምክንያት ሞት በሰው ላይ ሰለጠነ፤ በዳግማዊት ሔዋን (ድንግል ማርያም) መታዘዝ ምክንያት ሕይወት ወደ ዓለም መጣ። ሞት ኃይሉን አጣ።"

- **ቅዱስ ሄሬንዮስ**

"ተወዳጆች ሆይ! ስለ ቅዱሳን ሰማዕታት ብቻ የምትሰሙ አትሁኑ። እነርሱን ለመምሰልም ተጣጣሩ እንጂ። ለጊዜው ብቻ የምታደንቋቸው አትሁኑ። ወደ ቤታችሁ ብቻ ሳይሆን ወደ ልቡናችሁ ውሳጤም ዘልቀው እንዲገቡ አድርጉ። ዘወትር አስቧቸው። በልቡናችሁ ጓዳ እንዲገቡ አድርጓቸው። እናንተን ትተው ይሔዱ ዘንድ አትፍቀዱላቸው። ይህን ያደረጋችሁ እንደሆነ ዘወትር እያያችኋቸው ትበረታላችሁ። በእምነት ትጸናላችሁ። የለበሱትን የጽድቅ ጥሩር፣ የያዙትን ምግባረ ወንጌል፣ የእምነት ጋሻ፣ የመዳን ራስ ቁር፣ የመንፈስ ቅዱስንም ሰይፍ እየተመለከታችሁ ትበረታላችሁ።"

- **ቅዱስ ዮሐንስ አፈወርቅ**

"አንተ ሐሳብህን ልትመራዉ እንጂ፤ ሐሳብህ አንተን ሊመራ ቦታ አትስጠዉ፥ እዉነተኛ ክርስቲያን ስሜቱ የሚመራዉ ሳይሆን ስሜቱን የሚወመራ ነዉ።"

- **ብጹዕ ወቅዱስ አቡነ ሺኖዳ ሳልሳዊ**

ከምን ዓይነት ነገር መላቀቅ እንዳለብህ ታዉቃለህ ??

ብጹዕ ወቅዱስ አቡነ ሺኖዳ ሳልሳዊ ምድራዊ ምኞት ምን ያህል አስከፊ እንደሆነና እንዴት ከዚህ ነገር ነፃ መውጣት እንዳለብን እንዲህ በማለት ይመክሩናል፦

"ወዳጄ ከምድራዊ ምኞትህ ተላቀቅ ከምን አይነት ነገር መራቅ እንዳለብህ ታውቃለህ? ከምድራዊ ፍላጎት ከመሳሰሉት ራቅ ፍፁም የመንፈስ ነፃነት እንዲኖርህ ከፈለክ ከምድራዊ ምኞቶችህ ተላቀቅ።

በእርጋታና በግልጽነት ላውጋህ እጅግ አብዝተህ የምትጨነቅባቸው ልብህን የተቆጣጠሩት ታላላቅ ምድራዊ ተስፋዎች አሉህ።

እነኚህም ሃሳብህን ሁሉ ይቆጣጠሩታል ብቻህን በምቶንበት ጊዜ በምናብ ይመጡብሃል በምትተኛ ጊዜ ህልምህ ሁሉ ይህ ይሆናል ልትክዳቸው የማትችለው ነገር ግን የምታውቃቸው ምድራዊ አላማዎች አሉህ። ተፈላጊነት እንዲኖርህ ትመኛለህ፣ ስልጣን እንዲኖርህና፣ ኃያል እንድትሆን፣ ዕውቅና እንዲኖርህና ስምህ ከጽንፍ እስከ አጽናፍ እንዲናኝ ትፈልጋለህ።

በሀብት፣ በምድራዊ ስልጣን፣ በዕውቀት በማዕረግና በመልክ ዝነኛ የመሆን ተስፋ አለህ ፣ በመኖሪያ ቤት፣ በምግብ፣ በልብስና በሰውነት ደስታን በሚሰጡ ነገሮችም ተስፋ አለህ።

ዓለም በአንተ እንጂ አንተ በዓለም እየኖርክ አይደለም። ስለዚህ አንተነትህ በዚህ ምድራዊ ተስፋ የታጠረ ነው። መንፈስህም ከስጋ ፍላጎቶች መራቅን ትመኛለች ሥጋ በመንፈስ ላይ መንፈስ በሥጋ ላይ ይመኛልና። (ገላ.5፥17) እነዚህ ሥጋዊ ተስፋዎችና ፍላጎቶች ስኬታማ ስለማይሆኑ ግራ ትጋባለህ።

ይህን በእርግጥ ቅሬታን ያመጣብሃል።

እነዚህን ነገሮች ሁሉ ትናፍቃለህ ነገር ግን ናፍቆትህ አያስደስትህም። ስለዚህ ለምኞትህ ሁሉ ማስተካከያ ታበጅለት ይሆናል ምናልባትም ይጠቅሙኛል የምትላቸውን ሰዎች ማግኘት፣ በምኞትህ ዙሪያ የተጻፉ መዛግብት ማገላበጥ ትፈልግ ይሆናል በዚህም ላይ ታች ስትል ምኞትህን ለማሳካት ትታገላለህ እንዲሆን ሌላ ዘዴ ልትፈጥር ትችላለህ ይሁን እንጂ ሳይሳካልህ ቀርቶ በሃሳብና በጥረት ትታክታለህ ከዚያም ትበሳጫለህ። ከዚህ የከፋው ነገር በእነዚህ ምኞቶችና ተስፋዎች ስኬታማ አለመሆን ምክንያት ለከፋ ሕይወት መዳረግህ ነው።

እንደምትሰለች አውቃለሁ አዘንኩልህ እስከመቼ ድርስ በምኞት ማዕበል ውስጥ ትኖራለህ? የምትመኘውን ባገኘህ ጊዜ ደስተኛ ትሆናለህ ይህ ደስታ ስለማያረካህ ሌላ አዲስ ደስታን እንድትመኝ ያደርግሃል። ልክ ጌታ ኢየሱስ ክርስቶስ "ከዚህ ውሃ የሚጠጣ ሁሉ እንደገና ይጠማል" (ዮሐ.4፥13) እንዳለው እርካታ አይኖርህም።

ስለዚህ ውድ ወንድሜ ነገሩን በእርጋታ ከአንተ ጋር ለመነጋገር እፈልጋለሁ። "አለሙም ምኞቱም ያልፋል" (1ኛ ዮሐ.2፥17) ታዲያ ይህን ቃል ካወክ ለምን አለማዊ ፍላጎቶችን ለማግኘት ትታክታለህ? አንተ ልክ እንደ እኔ ለመሬት እንግዳ ነህ። ዓለም የሚያልፍበት

አንተም የምትጠፋበት ጊዜ ይመጣል ልክ ከእናትህ ማህጸን ራቁትህን እንደመጣህ እንደዚሁ ራቁትህን ትመለሳለህ።(ኢዮ. 1፥21)

ዓለምን ከነክብሯ ከነሀብቷና ከነስሟ ለቀሃት እንድትሄድ በመገደድ እንደ ማንኛውም ሰው ወደ መሬት ትወርዳለህ። ከዚያም ከዓለም ያገኘኸውን ደስታ ታወቂነት ወይም ምንም ይሁን ምን ሥጋህን ከሞት ሊከላከልልህ አልያም ሥጋን ከሚበሉት ትል ሊከላከልልህ አይችልም። በፍርድ ቀን ከዓለም ሀብትና ንብረት ውጭ በእግዚአብሔር ፊት ትቆማለህ። መልካም ይሁን ክፉ የሰራኸው ሥራ እንጂ የዓለም ቁሳዊ ነገር አይከተልህም።

ስለዚህ ውድ ወንድሜ ምኞትህንና ተስፋህን በዓለም ላይ በማድረግ መታወክህ ለአንተ ጥሩ አይደለም ይህችን ምድር እኾህንና አሜኬላን እንዳበቀለችልህ ትዘነጋለህን!!! ከእኛ በፊት የነበሩና ምድርን ሊረግጧት የማይገባት የቅዳሳን አባቶችና እናቶች አሠራርና ፈለግ ተከተል ቅድስናቸውን ያገኙት ይህችን ዓለም በመውደድ ሳይሆን በመናቅ ነበር ሁኔታዎች ሁሉ ተመቻችተውላቸው ሳለ በዓለም ስላሉ ነገሮች ለማንኛውም ጉጉት አልነበራቸውም ።

ውድ ወንድሜ አሁንም ምኞት አሉህ መዝገብህ ባለበት ልብህ ደግሞ በዚያ ይሆናልና (ማቴ.6፥21) የሥጋን ምኞቶችን ስለተቆራኘ መንፈሳዊ ነገሮች በአንተ አመለካከት ዋጋቸውን ያጣሉ ይህ የክብር ጌታ እንደተፈተነው ዓይነት ፈተና ነው። (ማቴ.4፥8-9)

አሁን አስተውል እነዚህን ነገሮችን ብትይዝ በጥሩ ምኞት ያላሰርካት ነፍስህን ብታጣ ጥቅሙ ምንድን ነው? ነፍስህ ነጻነትን ትሻለች።

ከስጋ ምኞት ተላቀን የመንፈስ ፍሬ የሆኑትን " የመንፈስ ፍሬ ግን ፍቅር፣ ደስታ፣ ሰላም፣ ትዕግሥት፣ ቸርነት፣ በጎነት፣ እምነት፣ የውሃት፣ ራስን መግዛት ነው።"(ገላ.5፥22) እንዳለው ብርሃነ ዓለም ቅዱስ ጳውሎስ እነዚህን ገንዘብ አድርገን እንድንኖር እግዚአብሔር አምላክ ይርዳን!!

(የብፁዕ ወቅዱስ አቡነ ሺኖዳ ሳልሳዊ "የመንፈስ ነጻነት "ከሚለውና በዲ/ን ደስታ ፍፁም ከተተረጎመው መጽሐፍ ላይ የተወሰደ። ምክር ወተግሳፅ እንዳቀረበው)

"የንስሀ አባት ማለት እርሱን ስትመለከት እግዚአብሔርን እና ትዕዛዛቱን የምታስታውስበት ሰው ማለት ነው።"

❖ ብጹዕ ወቅዱስ አቡነ ሺኖዳ ሳልሳዊ

መናፍቃን መነኮሳት በቤተክርስቲያን ውስጥ ሲሾሙ የሚያደርሱትን ጥፋት በተመለከተ ብፁዕ ወቅዱስ አቡነ ሺኖዳ ያስተላለፉት መልእክት ።

"እመኑኝ እጅግ አደገኛ ችግር የሚፈጠረው የፕሮቴስታንት እምነት ራሱ" ጥቁሩን የመነኮሳት ልብስ" ለብሶ ወደ ኦርቶዶክስ ቤተ ክርስቲያን የገባና ስራ የጀመረ እለት ነው።አንድም ፕሮቴስታንት ያማረ ሙሉ ልብስ ለብሶ ወደ እናንተ ሲመጣ ላትቀበሉት ትችላላችሁ። የመነኩሴ ልብስ ከለበሰ ግን እንደ አባት ነው የምታዩት።በዚህ ዘመን እየገጠመን ያለው አስከፊ

ችግርም ይኼው ነው።ሰዎች የኦርቶዶክስ ያልሆነ ትምህርትን በቤተክርስቲያን እያስፍፉ ነው።እንዲህ አይነት የኛ ያልሆኑ ትምህርቶች ወደ ቤተ ክርስቲያን ሰርገው ሲገቡ ልታገኙ ትችላላችሁ። ©

❖ 118 ኛው የግብጽ ፓትርያርክ ብፁዕ ወቅዱስ አቡነ ሺኖዳ ማልሳዊ ።

" ጨዋ ሰው በሌሎች ሰዎች መሳሳቆል ላይ የራሱን ምኞት አይገነባም እርሱ የሌሎችን ሰዎች ምኞት ለማደላደል የራሱን ምኞት ይረሳልና "

❖ ብፁዕ ወቅዱስ አቡነ ሺኖዳ

እዚህ ላይ ለመንፈሳዊ ሕይወት የሚጠቅም አንድ ቃል ልንገርህ! እግዚአብሔርን የምትወድ ከሆነ ታውቀዋለህ ። እግዚአብሔርን የምታውቀውም ከሆነ ትወደዋለህ። ከሁለቱ በአንዱ ጀምር ወደ ሌላው ትደርሳለህ።

ዓለም ከእግዚአብሔር ጋር ቢጣላ አካላዊ ቃል ዓለሙን ከራሱ ጋር ሊያስታርቅ ሰው ሆነ።

❖ *አቡነ ሺኖዳ*

✿የማታ ማታ መስቀሉ የሰው ልጆች ሁሉ መድሃኒት መሆኑን ቢያውቅ ኖሮ ሰይጣን ሳጥናኤል ከመጀመሪያውም ክርስቶስ ኢየሱስ ይሰቀል ዘንድ መስቀሉን አይተክልም ነበር::

❖ አበው ቀደምት

✿እመቤቴ ማርያም ሆይ..."ወለገጽኪ ይትመሐለሉ ኩሎሙ አሕዛብ ብዑላነ ምድር፤" (✿የምድር ባለጠጎች አሕዛብ ኹሉ በፊትሽ ይማለላሉ።) እንዳለሽ ቅዱስ ዳዊት እኔም ደግሞ በፀጉሬ ቁጥር ልክ አመሰግንሻለው!!!

➢ "ጸም የፀሎት ምክንያት ናት፤ የፀጋ ዕንብ መገኛ ናት፤ አርምሞን የምታስተምር ናት፤ ለበጎ ስራ ሁሉ ታነቃቃለች፤ የፀዋሚ ስጋው ምንጣፉን አንጥፎ ሌሊቱን ሁሉ ተኝቶ ማደር አይቻለውም በምን ጎኑ ይተኛዋል? ሰው አብዝቶ በጸመ ያህል በዚህ መጠን በትህትና ሁኖ እያለቀሰ ይፀልያል፤ ፀሎታት ከልቡናው ይታሰባሉ አንድም ፀሎተ ልብ ይሰጠዋል፤ በፊቱ የትእግስት ምልክት ይታያል በሃጢአቱ ያዝናል ክፉ ህሊና ይርቅለታል የበጎ ነገር መገኛ መከማቻ በምትሆን በጸም ይኖራልና፤ ጸምን የናቀ ያቃለለ ሰው በጎውን ነገር ሁሉ ከራሱ አራቀ።"

ማር ይስሃቅ

❖ ዝምታ ሃይማኖትን ትጠብቃለች ምግባርም ወደ ሰማያት ታወጣለች

ቅዱስ ያሬድ

✿"በበደል ምጣር የማትቈረጪ፣ ከ'ነጢአት ዐውሎ ነፋስ የተነጣ የማትነዋወጪ፣ ዘወትር ፍጹም የምትለመልሚ፣ በዘመኑ ኹሉ የምታፈሪ፣ በወሮች ኹሉ የምትለቀሚ፣ ከዕፅዋት ኹሉ ይልቅ የምታምሪ እመቤቴ ማርያም ሆይ! የተባረክሽ ዕፅ ነሽ።"

አባ ጊዮርጊስ ዘጋስጫ

"ወንድምህን አትናቀው"

- ወዳጄ ሆይ! ክርስቲያን ነህን? እንኪያስ በፍጹም ወንድምህን አትናቀው። እህትህን አትናቃት። ምንም ይሁን ምን ሰው አትናቅ ። ይህ የምትንቀው ወንድም በተለይ ክርስቲያን ከሆነ ክርስቶስን እየሰደብከዉ እንደሆን አስተውል ። "እንዴት"? ያልከኝ እንደሆንም ይህ የምትንቀው ወንድምህ የክርስቶስ ሕዋስ (ብልት) ሆኗልና። የክርስቶስ ሕዋስ ከኾነ ደግሞ እሱን ናቅከው ማለት ክርቶስን ናቅከው ማለት ነው። ወንድምህን የምትንቅ ከሆነም በጲላጦስ አደባባይ ጌታን ከገረፉት፣ እራቁቱን ከሰቀሉት፣ ሐሞትንና ከርቤን ቀላቅለው ከሰጡት፣ በፊቱ ላይም ከተፉበት ሰዎች በምንም አትተናነስም ። ስለዚህ ወንድምህን ከመናቅ ተጠንቀቅ ።
- ሃይማኖት ያለው ሰው ብኖር ምግባሩ ክፉ ከሆነ እነሆም ሃይማኖቱን ካደ የትምህርትንም ህግ አሰደበ ምግባር ሠርቶ ሃይማኖትን ካልተማረ ካላወቀ በምግባር ብቻ ሊጸድቅ ክርስቲያን ሊባል አይችልም

(ከቅዱስ ዮሐንስ አፈወርቅ)

ርዕሰ መነኮሳት አባ እንጦስ እንዲህ ይል ነበር፡-

- ✓ "ዘወትር በዐይንህ ፊት ፈሪሃ እግዚአብሔር ይኑር፤ ሕይወትና ሞት የሚሰጠውን ዘክረው። ዓለምንና በዓለም ያለውን ሁሉ ጥላው፤ ከሥጋ የሚመጣውን ደስታና ሰላም አትሻ፤ ለዚህኛው ኑሮ ሙትና ለእግዚአብሔር ሕያው ሁን፤ ለእግዚአብሔር ቃል የገባህውን አትርሳ፤ ያም በፍርድ ቀን ካንተ ይፈልግብሃል። ረኃብን በጸጋ ተቀበለው፤ ተጠማ፣ ተራቆተ፣ ንቁና በሐዘን የምትኖር ሁን። በልቡናህ አልቅስና ጩኽ፤ ለእግዚአብሔር የምትመች መሆን አለመሆንህን ፈትን፤ ሥጋህን ቀጥተህ ነፍስህን ታድናት ዘንድ።" ***(በበረሐው ጉያ ውሰጥ ገፅ 51)***
- ❖ "እግዚአብሔር የሚወዳችሁ አንድም እግዚአብሔርን የምትወዱት ወንድም እህቶቼ ሆይ! እግዚአብሔር በሥጋ ከባረከን በላይ በነፍስ የባረከን ይበልጣልና ስለዚሁ ልናመሰግነው ይገባናል፤ ምድራዊ መጠጥን አንድም ምድራዊ መብልን ከመስጠት መንፈሳዊ መጠጥንና መብልን መስጠት ይበልጣልና። እግዚአብሔር አስቀድሞ ለእሥራኤላውያን መናውን የሰጣቸው በኋላም እስራኤል ዘነፍስ ለምንባል ለእኛ ቅዱስ ሥጋዉንና ክቡር ደሙን የሰጠንም ስለዚሁ ነውና በሥጋ ከሰጠን ይልቅ በነፍስ የሰጠን ስለሚበልጥ እግዚአብሔርን እጅግ ልናመሰግነው ይገባናል።
- ❖ እግዚአብሔር በሥጋ ሲባርከን በዚያው (በሥጋዊው ነገር ላይ ብቻ) እንድንቀር አይደለም፤ የበለጠ ወደርሱ እንድንቀርብ ነው እንጂ። ሥጋዊውን ስጦታ ይዘን የምንቀር ከሆነ ግን ዓላማውን ስተናልና ልናስተካክል ይገባናል።
- ❖ ተወዳጆች ሆይ! በአፍአ ከተባረክነው ይልቅ በነፍስ የተባረክነው ይበልጣልና ስለዚያ እግዚአብሔርን ልናመሰግነው ይገባናል ብዬ እማልዳችኋለሁ። ለምን? መንፈሳዊው ነገር ከእኛ ዘንድ ካለ፥ ሥጋዊ ነገር ቢቀርም ምንም አናጣምና። መንፈሳዊውን ካጣን ግን ከእኛ ዘንድ ምን ተስፋ፥ ምንስ መጽናናት ይቀርልናል? አስቀድመን መንግሥቱንና ጽድቁን እንድንሻ የተፈለገውም ስለዚሁ ነው።
- ❖ የምወዳችሁ ልጆቼ! አስቀድመን እውነተኛውን ሀብት ይኸውም ሰማያዊውን ሀብት እንለምን፤ ርሱንም ለማግኘት እንጣጣር ብዬ እማልዳችኋለሁ። ሌላው ከዚያ በኋላ ይቀጥላል። እኛ ስለለመንን ሳይሆን ልቡናችን ዋናውን ስለፈለገ። ጸሎታችንን የምናገላብጠው ከሆነ ግን በነፍስ በሥጋ የተጐዳን እንሆናለን።"

(ቅዱስ ዮሐንስ አፈወርቅ)

- ❖ "እውነተኛ ክርስቲያን አባቱ ክርስቶስን ይመስላል። ይሰደዳል እንጂ አያሳድድም። ይሰደባል እንጂ አይሳደብም። የጠፉትን ፍለጋ ይደክማል እንጂ ይባስ ብሎ አይገፈትርም። በወንድሙ ውድቀት ያለቅሳል እንጂ አይደሰትም። እንዲህ ካልሆነ ግን አባቱ ሌላ ነው። ለእግዚአብሔር የምናቀርበው ምስጋና በጊዜውም ያለ ጊዜውም ሊሆን ይገባል። ባገኘን ጊዜ ብቻ ሳይሆን ባጣንም ጊዜ፤ ባለጤና በሆንን ጊዜ ብቻ ሳይሆን በታመምንም ጊዜ፤ ሲሳካልን ብቻ ሳይሆን ባልተሳካልንም ጊዜ ማመስገን መለማመድ አለብን። የምስጋናችን ምንጭ የሁኔታዎች መለዋወጥ ሳይሆን ስለ አምላካችን ብቻ ሊሆን ይገባዋል። ይህን ማድረግ ስንለማመድ በክብር ላይ ክብር ይጨመርልናል፤ እንደ

አባታችን ኢዮብ የዲያብሎስን አፍ እንዘጋለን። ተአምራትን ማድረግ ትፈልጋላችሁን?" እንኪያስ "በዘፈን የደነቆረን ጆሮ መዝሙር እንዲሰማ አድርጉት። ሴትን በመመኘት የታወረው ዐይን ፈጣሪውን እንዲያይ አድርጉት። በስርቆት የሰለለ እጅ በምጽዋት እንዲዘረጋ አድርጉት። ወደ ታጢአት ቤት በመሄድ ሸባ የሆነውን እግር ወደ እግዚአብሔር ቤት እንዲሮጥ አድርጉት። ሐሜትን በማውራት ዲዳ የሆነውን ከንፈር መልካም ንግግርን እንዲናገር አድርጉት። ከተአምራት ሁሉ የበለጠ ተአምር ይሄ ነው።"

<u>ቅዱሥ ዮሐንስ አፈወርቅ</u>

ብዙ አገልጋዮች የተሰጠንን ብዙ ነገር ትተን ትንሿን ነገር ለመጠበቅ ስንሮጥ ብዙ ጸጋዎቻችንን እናጣለን....ለመዘመር ብቻ ስንሯሯጥ ጸሎትን ስግደትን ትህትናን ወርውረን እንሰብራቸዋለን...ለመማር ብቻም ስንሮጥ ፍቅርን ቸርነትን ይቅርታን ወርውረን እንሰብራቸዋለን...አገልግሎት ብቻ ላይ ስንሮጥ ከጸሎት ሕይወት ፈጽመን እንወጣለን። ምን ለማለት ፈልጌ ነው"...ያለ ጸሎት ከሚሆን አገልግሎት ያለ አገልግሎት የሚደረግ ጸሎት የበለጠ ነው ..." ብለዋል አቡነ ሺኖዳ ሣልሳዊ ለማለት ነው።

<u>"አካሔድህን አስተካክል"</u>

<u>ቅዱስ ዮሐንስ አፈወርቅ</u>

"ከአፍቃሪያችን ክርስቶስ ያገኘነው ስጦታ እንዲህ ነው ተብሎ በቃላት መግለጥ የሚቻል አይደለም። እንዴት ያልን እንደሆነ እኛ በጎጢአት እየተንሯቀቅን ባለንበት ወራት እርሱ በምሕረቱ ጐብኝቶናልና። ጎጢአት ሸክም በሆነችብን ጊዜ እርሱ በእኛ ቦታ ተገብቶ ተሸክሞልናልና። በዚህ የማይለካ ፍቅሩ ከዲያብሎስ አገዛዝ ወደ መንግሥቱ አፈለሰን /ቈላ.1፡14/። እኛው ራሳችን ርቀን እርሱ ራሱ አቀረበን። እኛ ራሳችን በድለን እርሱ ካሠልን። ተወዳጆች ሆይ! ይህን ሁልጊዜ ከልቡናችን አናውጣ። የተሠጠንን ነጻ ሥጦታ አንዘንጋ። ከምን እንደወጣን አንርሳ።

ሰው ሆይ! የተጠራኸው ወደ ዘለዓለም ሕይወት ነው። የተጋበዝከው ወደ ልጁ መንግሥት ነው። ታድያ አንተእዚህ ስለምን ታንጠራራለህ? ስለምን እዚህ ትቀመጣለህ? ስለምን እዚህ ትንሯቀቃለህ? ስለ ሥጋህ ድሎት ብዙ ዋጋን ትከፍላለህ። ታድያ ስለ ነፍስህስ ትንሽ አይገድህምን? ወደ ሕይወት ተጠርተህ ሳለ ስለምን ወደ ሞት ትሮጣለህ? ቢያስፈለግ ይህ ያገኘኸው ስጦታ ላለማቆሸሽ ብዙ መሥዋዕትነትን መክፈል በተገባኽ ነበር። ብዙ ሰይፍን መታገሥ በተገባህ ነበር። ወደ እሳት እንኳ ብትጣል ስለ ድኅነተ ነፍስህ መቋቋም ይገባህ ነበር። ወዳጄ ሆይ! እስኪ ንገረኝ! የመንግሥተ ሰማያት ዜጋ ለመሆን ተጠርተህ ሳለ ራስህን የዚህ ዓለም ዜጋ ማድረግህ ስለምንድነው? እንደምን ያለ ስንፍና እንደያዘህስ ታስተውላለህን? ይህን ዓለም የመውደደህ ምስጢር ምኞትን መሻትህ ያሳያል። በዚህ ዓለም በምኞት መኖርን የሚሻ

ሰው ደግሞ ክርስቲያን መሆን፣ ክርስቲያን ተብሎ መጠራት፣ ክርስቶስን መስሎ መመላለስ ምኞት ሳይሆን እስር ቤት መስሎ ይታየዋል። ሁላችንም ወደዚሁ ቁጥ ካስገባን ሰነባብተናል። ከዚህች ዓለም ጋር የተወዳጀ ግን ምንም ክርስቲያን ቢባልም ምንም በአርባና በሰማንያ ቀኑ የሥላሴን ልጅነት ቢያገኝም ክርስቲያን ክርስቲያን መሽተቱ እየጠፋ ይሔዳል።በዚኽ ዓለም ወጥመድ ተቀፍድዶ ይያዛል።

ወዳጄ ሆይ! ይህን አድምጥና ፍርሐትና ረዓድ ይያዝህ!!! ምንም በቤተ መንግሥት ብትኖርም፣ ምንም በተሽቆጠቆጠ መኖርያ ቤት ብትኖርም እንደተመቸህ አድርገህ አትንገረኝ። አንተ የምትኖርበት ኑሮ ለእኔ ወጎኒ ቤት ነው፤ ያውም ሊፈርስ የተቃረበ ቤት!!! ይኽ ቤትህ ክረምት ሲመጣ ይፈርሳል። ክረምት (የመጨረሻይቱ ቀን) ስትመጣ ቤትህ ይፈርሳል። ክረምት ስላልኩህ ደግሞ "ለሁሉም ሰው ክረምት ከሆነበት እኔ ከማን እለያለሁ" ብለህ አታስብ፤ ይህቺ ቀን ለሁሉም ክረምት አትሆንምና። ዳግመኛም እግዚአብሔር ሌሊትና ቀን ብሎ ጠርቷታልና። ሌሊት የምትሆንባቸው ለኀጥአን ነው፤ ቀን የምትሆንላቸው ደግሞ ለጻድቃን ነው። እኔም ክረምት ብዬ መናገሬ ከዚህ አንጻር ነው። ሁላችንም ክረምት ሲመጣ መብረር እንችል ዘንድ በበጋው ላይ ካላደግን የገዛ እናቶቻችን እንኳ ቢሆኑ ትተዉን ይሔዳሉ እንጂ በዚያ ሰዓት እኛን መሸከም (ማዳን) አይቻላቸውም። የገዛ እናቶቻችን እንኳ በረሃብ እንሞት ዘንድ ትተዉን ይሔዳሉ። ቁጡ (ቤቱ) በላያችን ላይ ሲፈርስ እኛን መታደግ አይቻላቸውም። እግዚአብሔር ቤቱን ሲያፈርሰው፣ አሮጌው እንደ አዲስ ሲያደርገው፣ እያንዳንዱ እንዳልነበረ ሲሆን እኛን መርዳት የሚችል አንድ ስንኳ አይገኝም። የዚያን ጊዜ ጌታን በአየር ላይ መገናኘት የማይችሉቱ፣ የመንፈስ ክንፍ ተሰጥቶአቸው መብረር የማይችሉቱ ቤቱ በላያቸው ላይ ይፈርስባቸዋል። ስቃይ የስቃይም ስቃይ ይሆንባቸዋል። ስቃዩ የስቃይ ስቃይ ነው ማለቴ ከ እስከ የሚባል ስለሌለው ነው፤ ለዘለዓለም ስቃይ ስለሆነ ነው። ክረምት ብዬ መጥራቴ ስለዚሁ ነው፤ ኧረ እንደውም ከክረምት የባሰ ነው። እንዴት ያልከኝ እንደሆነ በዚሁ፡ክረምት ላይ የሚዘንበው ውኃ አይደለምና፤ እሳት እንጂ። በዚሁ ክረምት ዙርያህ ጨለማ የሚሆነው ከደመና ብዛት የተነሣ አይደለምና፤ ጽኑ ጨለማ እንጂ። የብርሃን ጭላንጭል የሌለው ጨለማ እንጂ። እዚህ የሚገቡት ሰዎች ተድላ መንግሥትን ማየት አይቻላቸውም፤ ሰማያትን ማየት አይቻላቸውም። ከመቃብር ውስጥ የባሰ ጨለማ ይውጣቸዋል እንጂ።

ወዳጄ ሆይ! አሁንስ አትርድምን? ወዴት እየሔድክ እንደሆነ አታስተውልምን? ፊትህንስ ወደ ልጁ መንግሥት አታደርግምን?"... አካሔድህን አስተካክል...

- እውነተኛ መነኩሴ በሁሉም ነገር ራሱን ይቆጣጠራል፣ ከማንም ጋር በሚነጋገርበት ጊዜ ከቁጣ ይሸሻል፣ ራሱን ይገዛል፣ አንድን ሰው ለማዳን በሚል ቢሆንም ከቁጣ ጋር ከተስማማ ግን ድኅነቱን አደጋ ላይ ይጥላል።

  /አባ መቃርስ/

- "እኛ ከተናገርን እግዚአብሔር ዝም ይላል፤ እኛ ዝም ስንል እርሱ ስራውን ይሰራል።"

  አቡነ ሽኖዳ

- በንስሐ ሕይወት ለመኖር የምንሻ ከሆነ ለወደቅንበት ኃጢአት ምክንያት መደርደር እና ለራሳችን ይቅርታን ለመስጠት መሞከር የለብንም።

  አቡነ ሽኖዳ ሳልሳዊ

አምላክ ልብህን ይቀይረዉ ዘንድ፣እርሱን ለመከተል ታገል። እንደዚህ በለዉ "ጌታ ሆይ ከልቤ አድነኝ፤ከሃጢያቴና ከተፈጥሮአዊ ዝንባሌም አድነኝ። ከአንተ በመታረቅ መንገዴ ላይ፣እነዚህ ነገሮች ሁሉ መሰናክል አይሁኑ።ብዙ ልቦችን፣ምናልባት ከእኔ በላይ የከፋ ሁኔታ ዉስጥ የነበሩትን፣ብዙ ሰዎችን ቀይረሃል።ከእነርሱ መሐል አንዱ እሆን ዘንድ እመኛለሁ፤ከቀየርካቸዉ ልቦች መሐልእንዱ አድርገኝ፤የሙሴ ጸሊምን፣እውጉስጢንን፣ግብጻዊቷ ማሪያምን፣አሪያኖስን ልብ ቀይረሃል።ታዲያ እኔ ያለሁበትን ሁኔታ ለመቀየር ይከብድሃልን?የእኔ ሁኔታ የተወሳሰበ መሆኑን ተመልከት!ነገር ግን በአንተወሰን በሌለዉ ሀይልህ ፊት ሲቀርብ ለመፍታት የሚያስቸግር አይሆንም። አምላኬ ሆይ የራሴን ልብ እንኳን ለመመለስና ሰላማዊ ለማድረግ አልችልም።ነገር ግን ከአንተ ጋር ለመታረቅ መጀመሪያ የሚያስፈልገኝን፤እንደዚህ ያለዉን ልቤን መቀየር የምትችለዉ አንተ ነህ። ለዚህ እርቅ ወደሚገባዉ፣ቅዱስ የሆነ ልብ መነካት ስሜት ልታመጣዉ የምትችለዉ አንተ ነህ። አምላክ ሆይ "ልጄ ልብህን ስጠኝ"(ምሳ.23፣26)በለኝ "ይሄዉ እንዳለ ዉሰደዉ" በሂሶጵ ረጭተህ አንፃኝ፤እጠበኝ ከበረዶም ይልቅ ነጭ እሆናለሁ። (ዳዊ.50(51)፣7) ልቤን እንድትጠግነዉ አይደለም የምጠይቅህ፣ንጹህ ልብን እንድትፈጥርልኝ (መዝ.51)አዲስ መንፈስ እንድትሰጠኝ እንጂ።(ሕዝ.36፣26) ለአንተ በልቤ ዉስጥ ፍቅር ባታገኝ፣ እባክህ ይሄንን ፍቅር ስጠኝ።ለአንተ

ፍቅር ቢጎድለኝ አትወቀሰኝ፤ እንደ ሐዋርያዉ ቃል ወደ ልቤ በመንፈስ ቅዱስ ፍቅርህን አፍስስብኝ እንጂ።(ሮሜ.5፣5)"የሚፈልግ" ነገር ግን የሚፈልገዉን ነገር እንዴት እንደሚያገኝ እነደማያዉቅ፤የሆነ ነገር የሚፈልግ ነገር ግን ማግኘት እንደማይችለዉ፤ህጻንልጅ ቁጠረኝ፤ በየመንገዱ እደነቃቀፋለሁና"በመንገድህ ምራኝ"(ዳዊ.119) ለድህነቴ ጉዳይ፣ስለ ነፍሴ ድህነት እንደሚገባኝ የቆረጥሁ ካልሆንኩኝ፣ የአንተ የእኔን ነፍስ ለማዳን መቁረጥህ በቂ ነዉ።የእኔ ፈቃድ ሀይል የእኔን ነፍስ ለማዳን በቂ ካልሆነ የአንተ ጸጋ በእርግጠኝነት ነፍሴን ሊያድናት በቂ ነዉ።በእኔ ክፉ ጸባዬ ከአንተ ጋር ለመኖር ፈቃደኛ ባልሆን አንተ ከእንተ ጋር እኖር ዘንደ መፍቀድህ በቂ ነዉ፤የአንተ ፈቃድ የሚያስፈገዉን ሁሉ ሊያደርግይችላልና።ጌታ ሆይ ለራሴ ፈቃድና ለድክመቴ ከተዉኝ ግን እጠፋለሁ። ራሱን ለማከምም ሆነ ወደ ሀኪምም ዘንድ መሄድ እንደማይችለዉህመምተኛ ሰዉ ቁጠረኝ፤ቃል ብቻ ተናገር ብላቴና ይፈወሳል።(ማቴ.8፣8)" ከልብህ ሆነ ለአምላክህ ጸሎት አቅርብ ጥረትህ እንደሚገበዉ ጥንካሬ ቢያጣ፤ጸሎትህ የጎደለዉን ይሞለዋል።"የጻድቅ ሰዉ ጸሎት በስራዋ እጅግ ሀይልን ታደርጋለችና።"(ያዕ.5፣16) ከአምላክ ጋር በመታረቅ ዉስጥ በራስህ ማስተወል አትደገፍ

ወይም በራስህ ሀይል ላይ"በፍጹም ልብህ በእግዚአብሔር ታመን።"(ምሳ.3፣5) ድካምህን የሚረዳ ሀይል ከአምላክ ጠይቅ!

አምላክ ከአንተ የሚፈልገዉ

☐ • ልብህን

☐ • ፈቃድህንና

☐ • እምነትህን ነዉ።

"ፈቃድ" ማለት ሀይለኛ ብርታትና ቁርጠኝነት ማሳየት አይደለም ግን ወደ አምላክህ ለመቅረብ ያለ ፍላጎት ነዉ እንጂ።የሰዉ ልጅ ደካማ ቢሆን እንኳን አምላክ ያደርግ ዘንድ ሀይል ይሰጠዋልና።በእርግጥ አምላክ ራሱ ያደርግዘንድ ጥንካሬ ይሰጠዋል፤አምላክ ራሱ በእርሱ ዉስጥ ይሰራል፤ ከእርሱ ጋርም ይሰራል።ቅዱስ ሐዋርያ ጳዉሎስ እንዳለዉ "ስለ በጎ ፈቃድ መፈለግንም ማድርግንም በእናንተ ዉስጥ የሚሰራ እግዚአበሔር ነዉና"(ፊል.2፣13) አምላክ ከእርሱ ጋር ለመታረቅ ያለህን ፍላጎት ይፈልጋል፤ምክንያቱም ማንንም ከእርሱ ጋር ይታረቅ ዘንድ አያስገድድምና። ይሄንን ፍላጎትህን ካስታወቅህዉ፤ከአንተ ጋር ሆኖ ይሰራል፤ለብቻዉ ያደርገዋል እያልኩኝ አይደለም።እንደዚህ ከሆነ አንድን ሰዉ ምንም ጥረት እንዳያደርግ ያበረታተዋልና። በሌላ በኩል ከእርሱ ጋር ለመስራት ያለህ ፍላጎት ለመታረቅ ምን ያህል የቆረጥክ መሆንህን ያሳያል፤እስካሁን ከእርሱ ጋር ለመታረቅ ከልብ ፍላጎትሊኖርህ ይገባል ብለናል።ለፍላጎትህ የቆረጥክ ስትሆን፣በጸሎት ተግባርህን ለመጀመር መሞከር አለብህ።ሊገጥመህ የሚችሉትን የትኛዉንም መሰናክል ሁሉም ድል ታደርግ ዘንድ እንዲረዳ መጸለይ አለብህ። የአባታችን በረከት ይደረብን፤ለእግዚአብሔርም ምስጋና ይሁን ለዘልዓለሙ አሜን።

- ራሱን የሚንቅ የሚያቃልል ሰው ከእግዚአብሔር ዘንድ እውቀትን ያገኛል አዋቂ ነኝ የሚል ሰው ከፈጣሪው ጥበብ ይለየዋል። **አረጋዊ መንፈሳዊ**

ተ□ ገንዘብን ማምለክ

ገንዘብ ብዙ ሰዎች የተንበረከኩለትና የተገዙለት በሰዎች ልቦና ውስጥም የእግዚአብሔርን አምላክነት የሚቀናቀን ጣዖት ነው ። ስለዚህም መድኃኒታችን ኢየሱስ ክርስቶስ በተራራው ስብከቱ " ለሁለት ጌቶች መገዛት የሚቻለው ማንም የለም ወይም አንዱን ይጠላል ሁለተኛውንም ይወዳል ። ለእግዚአብሔርና ለገንዘብ መገዛት አትችሉም ። " በማለት ነግሮናል ማቴ 6*24

ማንኛውም ሰው እግዚአብሔርን አመልካለሁ እያለ ገንዘብን ከተገቢው መጠን በላይ የሚያፈቅር ከሆነ ራሱን ያሞኛል ። ይህ ማለት የገንዘብ መገልገያነትን መቃወም ሳይሆን ገንዘብን በተገቢው መንገድ ጥቅም ላይ ማዋል እንጂ የገንዘብ ባርያ መሆን አይገባም ለማለት ነው ። ከዚህም ሌላ የገንዘብ አገልግሎትም ቢሆን ደግሞ ለአምልኮ ጣኦት መፈጸሚያ ፤ ለገቢረ ኃጢአት ከሆነ ገንዘብ አምላክ ሆኖ እየተመለከ ነው ማለት ይቻላል ።

በይበልጥ ደግሞ ገንዘባቸውን በአንዳንድ አገልግሎት ላይ ሳያውሉት በማከማቸት የሚረኩ ሰዎች ለገንዘብ የተገዙና ገንዘብን አምላካቸው ያደረጉ ናቸው ።እንደዚህ ዓይነት ሰዎች የሳንቲም ስባሪ እንድትወድቅባቸው የማይሹና በፈቃዳቸው ገንዘብን ለበጎ ምግባር የማያውሉ / የማይመጸውቱ / ናቸው ። እንዲህ የሚያደርጋቸውም ፍቅረ ንዋይ ነው ። ገንዘብን ከማንም በላይ ስለሚወዱ በራሳቸው ላይ ጣዖት አድርገው ያመልኩታል ። ለገንዘብ ያላቸው ፍቅርና አክብሮት ለፈጠራቸው ለእግዚአብሔርና በአርያ ሥላሴ ለተፈጠሩ ሰዎችም ከሚሰጡት ፍቅርና አክብሮት የበለጠ ነው ። ስለ ገንዘብ ብለው እግዚአብሔር አምላካቸውን የካዱ ፤ ወንድማቸውን የሚገድሉ ፤ እስከ ሞት ድረስም ራሳቸውን መሥዋዕት የሚያደርጉ እጅግ ብዙ ናቸው የእነዚህ ሁሉ አምላካቸው ገንዘባቸው ነውና ። ለዚህ ነው ገንዘብ መሰብሰብ ከሃይማኖቱና ከፍቅረ ሰብእ እንደሚለይ የሚያውቀው አምላክ " ለእናንተ በምድር ላይ መዝገብ አትሰብስቡ " በማለት ያስተማረው / ማቴ 6*19/

ስለሆነም ከአምልኮተ እግዚአብሔርና ከፍቅረ ቢጽ የሚለይ የገንዘብ ፍቅር ወደ ልቦናችን እንዳይገባና እንዳይሰለጥንብን ከፈጣሪያችንም ጋር እንዳያጣላን ልቦና ደጃችንን አጥብቀን ልንዘጋ በብርቱም ልንጠነቀቅ ይገባል ። ይህ ክፉ ጠላት ለመቋቋም የሚያስችለውን ኃይልና ጥበብ መንፈሳዊን አንዲሰጠን ዘወትር እግዚአብሔርን መለመን ያስፈልጋል ።

አንድ መንፈሳዊ አባት ልጃቸውን ሲመክሩ " ልጄ ሆይ ገንዘብ ካለህ በሥራ ላይ አውለው ገንዘብ ከሌለህ ግን ምንም ገንዘብ አትሰብስብ " በማለታቸው በፍቅረ ንዋይ የተነሣ የሚመጣው የኢጋንንት ጸር አደገኛ መሆኑን የሚያስገነዝብ ነው ። ጌታችን ኢየሱስ ክርስቶስ በገዳመ ቆሮንቶስ በዲያብሎስ በተፈተነ ጊዜ በፍቅረ ንዋይ የመጣበትን ፈተና በፀሊአ ንዋይ / ገንዘብን በመጥላት / ድል የነሣው መሆኑን እያሰብን በጥንቃቄ መኖር ያስፈልጋል ።

- ብጹዕነታቸው አቡነ ሺኖዳ ፫

† □፩ ከእኔ በቀር ሌሎች አማልክት አይሁኑልህ

[ዘጸ 20*3]

አንዳንድ ሰዎች ይህንን ትዕዛዝ በሚያነቡበት ወይም በሚሰሙበት ጊዜ "ይህ ከእኔ ጋር ምን ግንኙነት አለው ? ይህ ሊነገር የሚገባው ለከሐድያንና ለመናፍቃን ወይም ከሥጋዊ ዕውቀታቸው የተነሳ አለበለዚያም ከፍልስፍና በመነጨ ሁኔታ ከሃይማኖት ያፈነገጡትን ነው ። እኔ ግን በሳምንት ይህን ያህል ቀን እጸማለሁ አሥራት አወጣለሁ በየሰዓቱ እጸልያለሁ ከልብ ሆኜ እዘምራለሁ ፤ የቤተ ክርስቲያን መርሃ ግብሮችን ያለማቋረጥ እከታተላለሁ ስለሆነም ይህ ትእዛዝ አይመለከተኝም " ይሉ ይሆናል ።

ነገር ግን ይህ ትእዛዝ ሁሉንም የሚመለከት ነው ። ከእኔ በቀር ሌሎች አማልክት አይሁኑልህ " ተብሎ መነገሩ በሰው ልጅ እጅ የተጠረቡትንና የለዘቡትን ሰው ያቆማቸውንና በባሕር ወይም በፀሐይ ወይም በእሳት ወዘተ የተመሰሉትንና በተለያዩ ስያሜዎች የሚታወቁትን ጣኦታትን ብቻ ማለት አይደለም ።

በዚህ አንጻር ሰዎች ሀይላቸውን ያመልካሉ ፤ ገንዘባቸውን፤ ውበታቸውን ፤ ዝናቸውን ወዘተ ያመልካሉ ። እንዲህ አይነቶቹ ሰዎች በየፊናቸው የየራሳቸው ጣዖታትና አማልክት አሏቸው ማለት ነው ። እንደዚህም ሆነው እየኖሩ ደግሞ እነዚህ ሁሉ " በእውነት እግዚአብሔርን እናመልካለን በእርሱም እናምናለን ።" ሲሉ ይደመጣሉ ። በእነርሱ ዘንድ ግን እውነትም ሃይማኖትም ፈጽሞ የለም ።

- ***ብጹዕነታቸው አቡነ ሺኖዳ ሳልሳዊ !!***

"ምንኩስና ሕይወት ብርቱ ከሆነ ቤተክርስቲያንም ብርቱ ትሆናለች የምንኩስና ሕይወት መድከም የምጀምር ከሆነም ቤተክርስቲያንም እንዲሁ ትደክማለች"

- ሐዋርያው ቅዱስ አትናቴዎስ

ያወቅኸው መቼ ነው?

አንድን ሠው ስለ እርሱ የሚወራውን በመሥማት ወይም ከእርሡ ጋር የሥራ ግንኙነት ሥላለህ ልታውቀው አትችልም:: እያንዳንዱን ሠው በእርግጥ ምን እንደሚመስል የምታውቀው ከእርሡ ጋር ልዩነት ሲኖርህ ነው ::ይህ ልዩነት ደግሞ የአመለካከት ወይም የፍላጎት ተቃርኖ ሊሆን ይችላል::

(ከቅዱሥነታቸው አቡነ ሺኖዳ ሣልሣዊ የህይወት ልምድ መፅሀፍ የተወሠደ)

- **<u>ይቅርታ ማድረግ</u>**

"ይቅርታ ማድረግ ተሸናፊነት አይደለም አሸናፊው እግዚአብሔር በመስቀል ላይ ሆኖ ይቅርታን ያደረገውም ኃይል አጥቶ አልነበረም። ሁሉንም ስለ ድፍረታቸውና ንቀታቸ በቅጽበት ሊያጠፋቸው ይቻለው ነበረ እንደ ባብሎን ስዎች ሰቃዮቹን በቋንቋ እንዳይግባቡ ማድረግም ይችል ነበረ። እርሱ እንኳን. ባያደርገው በድንጋጤና በመደመም ፈዝዘው የሚመለከቱትን የሰማይ ኃይላት ቅዱሳን መላእክቱን ሊያዝዛቸው ይችል ነበረ "ወይስ አባቴን እንድለምን እርሱም አሁን ከአሥራ ሁለት ጭፍሮች የሚበዙ መላእክት እንዲሰድልኝ የማይቻል ይመስልሃልን? " ማቴ 26: 53 እንዳለው ወደ አባቱ "ይቅር በላቸው" ብሎ በመለመን ፈንታ ለጥፊት የታዘዙ መላእክትን መጥራት ይችል ነበረ። በእርግጥ በመስቀሉ ዙሪያ ያሉ ጠላቶቹን ለማጥፋት የመላእክት ጭፍራ አያስፈልግም አንዱ መላአክ ቅዱስ ሚካኤል መቶ ሰማንያ አምስት ሽህ የሰናክሬምን ሠራዊት ሰይፍ እንኳን ሳይመዝዝ በግርማው ብቻ እንደ ቆሎ አርግፎአቸው እንደነበር አይረሳም (2ኛ ነገሥ 19:35)የሚካኤል ጌታ ኢየሱስ ክርስቶስ ግን ሠራዊተ መላእክቱ በዚያች ዕለት እንዲዘምቱ አልወደደም። በዚህ ምክንያት ያቺ ዕለት ለመላእክቱ አስጨናቂ ዕለት ነበረች።

- ሕማማት ገፅ 335

‹‹ነቢይ ዳዊትም ነፍሴን በሲኦል አትተዋትም የባሕርይ ልጅህንም ሙስና መቃብርን ያይ ዘንድ አሳልፈህ አትሰጠውም አለ። ይህም ጌታ በተዋሐደው አካል ያለውን የነፍስና የሥጋ ተዋሕዶ ያስረዳልኀ የቀና ልቡና እውቀት በእርሱ ጸንቶ ይኖር ዘንድ። ዳዊት እንደተናገረው እውነት ሆነኀ ነፍስ መለኮትን ተዋሕዳ ወደ ሲኦል ወርዳለችናኀ ሥጋም ሦስት መዓልት ሦስት ሌሊት በመቃብር ሳለ መለኮት ከሥጋ አልተለየም። አምላክ ሰው የመሆኑን እውነትነት ያስረዳ ዘንድ፣ መለኮት ነፍስን ተዋሕዶ በአካለ ነፍስ የሲኦል ምሥጢርን ገልጦ ፈጽሟልናኀ በሲኦልም በቁራኝነት አልተያዘምና።››

- **ቅዱስ ኤጲፋንዮስ ዘቆጵሮስ**

‹‹ታመመ ሞትን ከተቀበለበት ከሥጋ ጋር ተዋሕዶ በመስቀል ላይ በፈቃዱ ለሥጋውያን ሞተኀ ባሕርየ መለኮት ሥጋን ተዋሕዶ በማኅፀን ካደረ ጀምሮ ሥጋ ገንዘቡ እንደመሆኑ በሥጋ ይኸንን ሥርዐት ፈጸመ።

ለማይመረመር ለመለኮቱ ባሕርይ እንደሚገባ ደግሞ እርሱ ኀብስት አበርክቶ ሁሉን ያጠግባልኀ አይራብምኀ አይጠማምኀ አይደክምምኀ አያንቀላፋምኀ አይታመምምኀ አይሞትምኀ ሕይወትን

ለሁሉ ይሰጣል። ዳግመኛ በዛ በሲኦል ተገዝተው ያሉ ነፍሳትን ያድን ዘንድ በአካለ ነፍስ ወደ ሲኦል ወረደ በመለኮቱም ሲኦልን በዘበዘ››

- ቅዱስ ቄርሎስ ዓምደ ሃይማኖት (ዘእስክንድርያ)

"አዳምን የፈጠሩ እጆቹ በመስቀል ቀኖች ተቸነከሩ ወዮ በገነት የተመላለሱ እግሮች በመስቀል ቀኖች ተቸነከሩ ወዮ የማይሞተው ሞተ ሞትን ይሽረው ዘንድ ሞተ ሙታንን ያድናቸው ዘንድ ሞተ የምትወዱት ሰዎች ፈጽሞ አልቅሱለት።"

- ቅዳሴ ዮሐንስ አፈወርቅ

✍ በትጋህ ሌሊት ጊዜ መቆም መስገድ ባይቻልህ በአልጋህ ላይ ተቀምጠህ ሳለህ ትጋህን ይዝ ተገኝተህም ቢሆን ሁለት ቀን ወይም ባይቻልህ እስከ ሠርክ ጹም ። እስከ ሠርክም ወይም ባይቻልህ መጥነህ ተመገብ እስክትጠግብ እንዳትመገብ ተጠበቅ

- አቡነ ሺኖዳ

"ክፉ ሰው ክፋትን ለመስራት ደፍሮ ሲሄድ መልካም ሰው በጎ ነገር ለማድረግ ፈሪ ሆነ"

- አቡነ ሺኖዳ ሦስተኛ

<u>ብሂለ አበው</u>

☞ ‹‹እግዚአብሔር ሆይ አፈርና ትቢያ ሆኜ ሳለ ጻድቅ አድርገው ከሚቆጥሩኝ ሰዎች አድነኝ››

/አባ እንጦንስ/

☞‹‹ፍጡራንን መርምሮ ማወቅ ካልተቻልን ሁሉን የፈጠረ እርሱን መርምሮ ማወቅ እንደምን ይቻልናል››

/ቅዱስ አትናቴዎስ/

☞ ‹‹ወርቅ በእሳት እንደሚፈተን ሁሉ የክርስቶስንም ፀጋና ክብር ሳይፈተኑ ማግኘት አይቻልም የዚህ ዓለም ፈተናና እሳት ቶሎ ያልፋል ይጠፋል ኃጢያተኞች የሚገቡበት የገሃነም እሳት ግን ለዘላለም እንደ ነደደ ይኖራል››

/ቅዱስ ሚናስ/

☞‹‹በማንም ላይ ክፋትን አትስሩ አትፍረዱ ይህንን ከጠበቃችሁ ርስቱን ትወርሳላችሁና››

/ታላቁ አባ መቃርስ/

☞ ‹‹ብዙ ጊዜ ብዙ እናገራለሁ በመናገሬም አዝናልሁ በዝምታዬ ግን ያዘንኩበት ጊዜ የለም››

/ቅዱስ አርሳንዮስ/

☞ ‹‹ቤተክርስትያን መጠጊያችን ነች ቤተክርስትያን የኖኅ መርከብ ነች በውስጧ እንጠለላልን ከውጭዋ ግን ማዕበልና ቀላያት ተከፍተዋል››

/ቅዱስ እንድርያስ/

☞ ‹‹ልባችንን ጠፊና በስባሽ ከኾነው ከምድራዊው ምኞት አርቀን ከበደል በንስሐ ነጽሕ ካደረግነው በጸጋ መንፈስቅዱስ የተሞላን እንሆናለን››

/አባ አብርሃም መፍቀሬ ነዳያን/

☞ ‹‹ስጋዊ ፍላጎቶችን ማሸነፍ ለአክሊለ ህይወት የሚያበቃ ሰማዕትነት ነው››

/ብፁዕ አቡነ ጎርጎርዮስ ካልዕ/

☞ ‹‹የቤተክርስቲያን ህይወት በመስቀል ላይ ስለሆነ ፈተና ይበዛበታል ስለዚህ ከግል ህይወታችሁ ይልቅ የቤተክርስቲያናችሁን አቋም አጠንክሩ››

/ብፁዕ አቡነ ጎርጎርዮስ ካልዕ/

☞‹‹ከመኝታህ በፊት የምታደርገውን ፀሎት ትተህ እንድትተኛ መንፈስህ ሲገፋፋህ እሺ ብለህ አትቀበለው። እንዲያውም መዝሙረ ዳዊትን ጨምርና ሌሊቱን በሙሉ ስትፀልይ እደር››

/ቅዱስ ይስሀቅ ሶርያዊ/

☞ ‹‹ኃጥያታችንን እኛ እያሰብን የምንፀፀት ከሆነ እግዚአብሔር ይረሳልናል ኃጥያታችንን እኛ እረስትን የምንፅናና ከሆነ እግዚአብሔር ያስብብናል››

/ቅዱስ እንጦስ/

የአባቶቻችን ጸጋና በረከት ከሁላችን ጋር ይሁን::

እምነትና ሥራ

ሐዋርያ ጳውሎስ "አብርሃም በእምነት ፀደቀ" (ሮሜ 4) ሲል ይናገራል፤ በሌላ ቦታ ሐዋርያ ያእቆብ "አብርሃም በስራ ፀደቀ" (ያዕ 2) ሲል ደግሞ ይናገራል። ጳውሎስ "በስራ ልትፀድቁ የምትሹ ዋጋ የላችሁም" ይላል፤ ያእቆብ ደግሞ "ያለስራ በእምነት ብቻ መፅደቅ የምትሹ ከዲያቢሎስም አትሻሉም" በማለት ይናገራል:: ይህ ምንድን ነው? እርስ በእርሱ ይጋጫልን? ነገር ግን አይደለም ጳውሎስ ወደ ክርስቶስ በእምነት ላልቀረቡት አይሁድ ስለእምነት መሰረትነት አስተማረ ያእቆብ ደግሞ ክርስቶስን አውቀው በምግባር ክርስቶስን ላልመሰሉት በስም ብቻ ክርስቲያኖች ለሆኑት የምግባርን ጣራና ግድግዳነት አስተማረ።ጳውሎስ ያልቀረቡትን ያቀርብ ዘንድ የወተትን ቃል አቀበለ ያእቆብ የቀረቡት ይፀኑ ዘንድ የስጋ ምግብን አዘጋጀ። ሁለቱም ግን በጎችን ወደ እረኛቸው ሳቡ እንዲህም ነው እምነት መሰረት ነው ምግባር ደግሞ ጣራና ግድግዳ ነው።

ለአንዳንዶች የተጋጨ ቢመስል የተጋጨ አይደለምና የኦርቶዶክስ ቤተክርስቲያን ይህን ልዩ ምስጢር አብራርታ ለሚጠይቋት ሁሉ መልስ ትሰጣለች።

ተወዳጆች ሆይ! አንድ እንግዳ ወደ ቤታችን ሲመጣ ቤታችንን እንደምን እንደምናሰናዳው ሁላችንም እናውቀዋለን። ሁላችንም እንግዳችንን ደስ የሚያሰኘው ነገር ለማድረግ የምንቻኮል አይደለንምን? ለእንግዳችን የሆነ ነገር ባናደርግለት፥ እንግዳችን በመምጣቱ ደስ ተሰኝተን እርሱን ደስ የሚያሰኝ ነገር ባናደርግለት፥ ግን ደግሞ በመምጣቱ ደስ እንደተሰኘን ብንነግረው እንግዳችን በፍጹም አያምነንም። በእንግዳችን መምጣት ደስ እንደተሰኘን ከቃላት ባለፈ በገቢር መግለጥ አለብንና። እንኪያስ የዓለም መድኃኒት ኢየሱስ ክርስቶስ ወደ ሕይወታችን ከመጣ ደስ መሰኘታችንን በገቢር ልንገልጽ ያስፈልጋል። እንግዳችን ክርስቶስን የሚያስቈጣ ነገር ልንፈጽም አይገባንም።

እንግዳ ሲመጣ ቆሻሻ ልብስ አይለበስም። እንግዳ ሲመጣ የሚያስጸይፍ ነገር አይነገርም። ክርስቶስ በሕይወታችን ውስጥ እንዲኖር ስንፈልግም ቆሻሻ ልብሳችንን (ማንነታችንን) አውልቀን ልንጥል ያስፈልጋል፤ አስጸያፊ ነገራችንን ልንተው ያስፈልጋል። እንግዳ ሲመጣ ቤት ያፈራው ሁሉ ይቀርብለታል። ክርስቶስ ወደ ቤታችን ሲመጣም የሚበላ ነገር ልናቀርብለት ይገባል። ለመሆኑ የክርስቶስ መብል ምንድነው? ጌታችን ኢየሱስ ክርስቶስ ይህን ጥያቄ ሲመልስልን እንዲህ ብሏል፦ "የእኔስ መብል የላከኝን ፈቃድ አደርግ ዘንድ ሥራውንም እፈጽም ዘንድ ነው" ዮሐ.፬፡፴፬።

እንኪያስ ክርስቶስ የራበው ይኸው ነውና እንመግበው፤ ኢየሱስ የጠማው ይኸው ነውና እናጠጣው። እርሱም ይቀበለናል። አንዲት ኩባያ ቀዝቃዛ ውኃ ብንሰጠው እንኳ ይቀበለናል። ስለብዛቱ ሳይሆን ስለፍቅሩ ብሎ ይቀበለናል። እኛን ስለመውደዱ ይቀበለናል። የምንወደው ሰው የሰጠነውን የሚቀበለን ስለ መጠኑ አይደለም፤ ስጦታው የወዳጅ ስለሆነበት እንጂ። ሰው ወዳጁ ጌታም ሁለት ሳንቲም ብንሰጥ እንኳ ብዙ እንደሰጠን አድርጐ ይቀበለናል። ጌታችን ኢየሱስ ክርስቶስ ስጦታችንን የሚቀበለው ድሃ ስለሆነ አይደለም። ጌታችን ኢየሱስ ክርስቶስ የድሃውም

የባለጸጋውም ስጦታ እኩል የሚቀበለው ስለ ልቡናችን ኀልዮት (Intention) እንጂ ስለ ስጦታው ትልቅነት ወይም ዋጋ አይደለም። ስለዚህ ክርስቶስን እንደምንወደው ለመግለጽ የግድ ብዙ ወይም በውድ ዋጋ የተገዛን ስጦታ መስጠት አያስፈልገንም። ስጦታችን እርሱ ወደ እኛ ስለመጣ ደስ የመሰኘታችን መግለጫ ነውና ስለ ስጦታችን መጠን ልንመለከት አይገባም።

- ቅዱስ ዮሃንስ አፈወርቅ

ደጉ ሳምራዊ

ደጉ ሳምራዊ የኢየሱስ ክርስቶስ ምሳሌ ነው። ሳምራዊ ማለት ሀገር ጠባቂ ማለት ነው፥ እየሱስ ክርስቶስም እረኛችን ጠባቂያችን ነው፤ ዮሐ 10፥11 ፣1ኛ ጴጥ 2፥24። ሀገር ጠባቂ ሀገርን የሚጠብቀው ራሱን ለሞት አሳልፎ በመስጠት ነው፥ እየሱስ ክርስቶስም እኛን በነፍስም በሥጋም የጠበቀን ራሱን ለመስቀል ሞት አሳልፎ ሰጥቶ ነው፤ ደጉ ሳምራዊ ቍስለኛውን በሩቅ አይቶ አዘነለት ፥ቀርቦም በቍስሉ ላይ ወይንና ዘይት አፈሰሰለት፤ ወይኑ የቍስለኛውን ደም እንዲያቆምለት እንዲያደርቅለት ነው። ቍስል ቶሎ የሚደርቀው ከላይ ነው፥ ወዲያውም እየተሰነጣጠቀ ያሰቃያል፤ ለዚህም መከላከያ እንዲያለሰልስለት ዘይቱን አፍስሶለታል። ጌታችንም በሩቅ ማለትም በሰማይ መንበሩ ተቀምጦ ቍስለኛውን አዳም በዓይነ ምሕረቱ አየው፥ ገጸ ምሕረቱን መለሰለት፤ ቀረበውም። (ባሕርዩን ባሕርይ አደረገ ፥ የባሕርዩ መመኪያ ከሆነች ከድንግል ማርያም ከሥጋዋ ሥጋ ከነፍሷም ነፍስ ነስቶ፥ ተዋሕዶ ሰው ሆኖ ተወለደ)። ወይን እንደማፍሰስ፡በመልዕልተ መስቀል ተሰቅሎ፥ ሥጋውን ቆረሰለት ደሙን አፈሰሰለት። ጌታችን የጸሎተ ሐሙስ ዕለት ወይኑን በጽዋ አድርጎ፡ «ሁላችሁ ከእርሱ ጠጡ፤ ስለ ብዙዎች ለኃጢአት ይቅርታ የሚፈስ የአዲስ ኪዳን ደሜ ነው፤» ያለው ለዚህ ነው። ማቴ 26፥27።

እንደ ዘይት ደግሞ የመንፈሰ ቅዱስን ጸጋ ሰጥቶታል። ይኸንን በተመለከተ ቅዱስ ዳዊት፡«ወይን (የክርስቶስ ደሙ) የሰውን ልብ ደስ ያሰኛል፥ ዘይትም ፊትን ያበራል፥ (መንፈሰ ቅዱስ ሰውን ብሩኅ መልአክ ያስመስለዋል) ፥ እህልም (የክርስቶስ ስንዴ ሥጋው) የሰውን ጉልበት (ነፍስን) ያጠናክራል።» ብሏል። መዝ 103፥15 ሐዋርያው ቅዱስ ዮሐንስም፡ «እናንተም ከቅዱሱ ቅባት ተቀብላችኋልና ሁሉንም ታውቃላችሁ።» ያለው ጸጋ መንፈሰ ቅዱስን ነው።

ደጉ ሳምራዊ ከአህያው ወረዶ ቍስለኛውን ማስቀመጡ የሚያመለክተው፡ ጌታችን ኢየሱስ ክርስቶስ ከሰማይ መንበሩ መውረዱንና የአዳምን በሰማይ መንበሩ ማስቀመጡን ነው። ሐዋርያው ቅዱስ ጳውሎስ፡ «በኢየሱስ ክርስቶስ በሰማያዊ ሥፍራ ከእርሱ ጋር አስቀምጠን፤» ያለው ይኸንን ምሥጢር ይዞ ነው። ኤፌ 2፥7። ምክንያቱም በተዋሕዶ አምላክ የሆነ ሥጋ በሰማይ የእሳት መንበር ተቀምጧልና።

ደጉ ሳምራዊ፡ ያከመውን ቍስለኛ ለእንግዶች ቤት ጠባቂ ማስረከቡ፥ ኢየሱስ ክርስቶስ በደሙ ፈሳሽነት ያከማቸውን ምእመናን ለመምህራን የማስረከቡ ምሳሌ ነው።ቅዱስ

ጴጥሮስን፦«ግልገሎቼን አሰማራ፥ ጠቦቶቼን ጠብቅ ፥ በጎቼን አሰማራ፤» ያለው ለዚህ ነው። ዮሐ 21፥15። ሁለት ዲናሮች ደግሞ የሁለቱ ማለትም የብሉይ ኪዳንና የአዲስ ኪዳን መጻሕፍት ምሳሌዎች ናቸው። የሰው ሕይወቱ የሚጠበቀው

በእነዚህ ነውና። በሁለት ዲናር የተመሰሉ ቅዱሳት መጻሕፍት ምግበ ነፍስ ናቸውና። ቅዱስ ዳዊትም፦ «ቃልህ ለጉሮሮዬ ጣፋጭ ነው፤ ከማርና ከወለላ ይልቅ ጣፈጠኝ።» ብሏል። መዝ 118፥103።

ደጉ ሳምራዊ የእንግዳ ቤት ጠባቂውን፦ «ከሁለት ዲናር በላይ ብታወጣ እኔ በተመለስኩ ጊዜ እከፍልሃለሁ፤» አለው እንጂ፥ «ዋጋ የለህም፤» አላለውም። ይህም የሚያመለክተው፦ መምህራን የተሰጣቸውን፦ ሁለት ዲናር (ብሉይ ኪዳንን እና አዲስ ኪዳንን) ይዘው ፥ የምእመናንን ሕይወት ለመጠበቅ ሌሎች ቅዱሳት መጻሕፍትን ቢጽፉ፥ ጌታ ሲመጣ የድካማቸውን ዋጋ እንደሚከፍላቸው ነው። ቅዱሳን ሊቃውንት፦ መጽሐፍ ቅዱስን ለማብራራት ፥ ንባቡን በመተርጐም ፥ ምሥጢሩን በማራቀቅ አያሌ መጻሕፍትን ጽፈዋል። እነዚህም አዋልድ መጻሕፍት ይባላሉ። የቅዱሳት መጻሕፍት ልጆች ማለት ነው። የገድል የድርሳን እና የተአምር መጻሕፍት ቍጥርም ከአዋልድ መጻሕፍት ነው። እነርሱም የእግዚአብሔር ሰዎች የእግዚአብሔርን ቃል እንዴት እንደፈጸሙ፥ መንፈሳዊ ሕይወታቸውን የሚያሳይ ነው። መጻፍ ማጻፍም ፥ መስማት ማሰማትም ዋጋ አለው። እንግዲህ በተሰጡን ሁለት ዲናሮች ሥራ እንድንሠራ ፥ ሌሎችንም ቅዱሳት መጻሕፍት በመጻፍና በማጻፍ እንድንመክርና እንድንመክር ፥ የተሰጠንን አደራ እንድንጠብቅ ፥ በዚህ ዓለም ተዋርደን ምእመናን የሚከብሩትን ግብር ይዘን እንድንገኝ፥ የሚያዝን ልቡና እንዲሰጠን ፥ የምናቆስል ሳይሆን የቆሰሉትን የምናክም እንዲያደርገን፥ የእግዚአብሔር ቸርነት የድንግል ማርያም አማላጅነት አይለየን አሜን።

ብሒሳተ አበው ዘኦርቶዶክስ ተዋህዶ:

"አካሔድህን አስተካክል"

ቅዱስ ዮሐንስ አፈወርቅ

"ከአፍቃሪያችን ክርስቶስ ያገኘነው ስጦታ እንዲህ ነው ተብሎ በቃላት መግለጥ የሚቻል አይደለም። እንዴት ያልን እንደሆነ እኛ በኀጢአት እየተንቈቀቅን ባለንበት ወራት እርሱ በምሕረቱ ጐብኝቶናልና። ኀጢአት ሸክም በሆነችብን ጊዜ እርሱ በእኛ ቦታ ተገብቶ ተሸክሞልናልና። በዚህ የማይለካ ፍቅሩ ከዲያብሎስ አገዛዝ ወደ መንግሥቱ አፈለሰን /ቈላ.1፡14/። እኛው ራሳችን ርቀን እርሱ ራሱ አቀረበን። እኛ ራሳችን በድለን እርሱ ካሠልን። ተወዳጆች ሆይ! ይህን ሁልጊዜ ከልቡናችን አናውጣ። የተሠጠንን ነጻ ሥጦታ አንዘንጋ። ከምን እንደወጣን አንርሳ።

ሰው ሆይ! የተጠራኸው ወደ ዘለዓለም ሕይወት ነው። የተጋበዝከው ወደ ልጁ መንግሥት ነው። ታድያ አንተ እዚህ ስለምን ታንጠራራለህ? ስለምን እዚህ ትቀመጣለህ? ስለምን እዚህ ትንቈቀቃለህ? ስለ ሥጋህ ድሎት ብዙ ዋጋን ትከፍላለህ። ታድያ ስለ ነፍስህስ ትንሽ አይገድህምን? ወደ ሕይወት ተጠርተህ ሳለ ስለምን ወደ ሞት ትሮጣለህ? ቢያስፈልግ ይህ ያገኘኸው ስጦታ ላለማቆሸሽ ብዙ መሥዋዕትነትን መክፈል በተገባኸ ነበር። ብዙ ሰይፍን መታገሥ በተገባህ ነበር። ወደ እሳት እንኳ ብትጣል ስለ ድኅነተ ነፍስህ መቋቋም ይገባህ ነበር። ወዳጄ ሆይ! እስኪ ንገረኝ! የመንግሥቱ ሰማያት ዜጋ ለመሆን ተጠርተህ ሳለ ራስህን የዚህ ዓለም ዜጋ ማድረግህ ስለምንድነው? እንደምን ያለ ስንፍና እንደያዘህስ ታስተውላለህን? ይህን ዓለም የመውደደህ ምስጢር ምኞትን መሻትህ ያሳያል። በዚህ ዓለም በምኞት መኖርን የሚሻ ሰው ደግሞ ክርስቲያን መሆን፣ ክርስቲያን ተብሎ መጠራት፣ ክርስቶስን መስሎ መመላለስ ምኞት ሳይሆን እስር ቤት መስሎ ይታየዋል። ሁላችንም ወደዚሁ ቁጥ ካስገባን ሰነባብተናል። ከዚህች ዓለም ጋር የተወዳጀ ግን ምንም ክርስቲያን ቢባልም ምንም በአርባና በሰማንያ ቀኑ የሥላሴን ልጅነት ቢያገኝም ክርስቲያን ክርስቲያን መሸተቱ እየጠፋ ይሔዳል።በዚኽ ዓለም ወጥመድ ተቀፍድዶ ይያዛል።

ወዳጄ ሆይ! ይህን አድምጥና ፍርሐትና ረዓድ ይያዝህ!!! ምንም በቤተ መንግሥት ብትኖርም፣ ምንም በተሸቆጠቆጠ መኖርያ ቤት ብትኖርም እንደተመቸህ አድርገህ አትንገረኝ። አንተ የምትኖርበት ኑሮ ለእኔ ወጎኒ ቤት ነው፤ ያውም ሊፈርስ የተቃረበ ቤት!!! ይኽ ቤትህ ክረምት ሲመጣ ይፈርሳል። ክረምት (የመጨረሻይቱ ቀን) ስትመጣ ቤትህ ይፈርሳል። ክረምት ስላልኩህ ደግሞ "ለሁሉም ሰው ክረምት ከሆነበት እኔ ከማን እለያለሁ" ብለህ አታስብ፤ ይህቺ ቀን ለሁሉም ክረምት አትሆንምና። ዳግመኛም እግዚአብሔር ሌሊትና ቀን ብሎ ጠርቷታልና። ሌሊት የምትሆንባቸው ለኀጥአን ነው፤ ቀን የምትሆንላቸው ደግሞ ለጻድቃን ነው። እኔም ክረምት ብዬ መናገሬ ከዚህ አንጻር ነው። ሁላችንም ክረምት ሲመጣ መብረር እንችል ዘንድ በበጋው ላይ ካላደግን የገዛ እናቶቻችን እንኳ ቢሆኑ ትተዉን ይሔዳሉ

እንጂ በዚያ ሰዓት እኛን መሸከም (ማዳን) አይቻላቸውም። የገዛ እናቶቻችን እንኳ በረሃብ እንሞት ዘንድ ትተዉን ይሔዳሉ። ቁጡ (ቤቱ) በላያችን ላይ ሲፈርስ እኛን መታደግ አይቻላቸውም። እግዚአብሔር ቤቱን ሲያፈርሰው፣ አሮጌው እንደ አዲስ ሲያደርገው፣ እያንዳንዱ እንዳልነበረ ሲሆን እኛን መርዳት የሚችል አንድ ስንኳ አይገኝም። የዚያን ጊዜ ጌታን በአየር ላይ መገናኘት የማይችሉቱ፣ የመንፈስ ክንፍ ተሰጥቶአቸው መብረር የማይችሉቱ ቤቱ በላያቸው ላይ ይፈርስባቸዋል። ስቃይ የስቃይም ስቃይ ይሆንባቸዋል። ስቃዩ የስቃይ ስቃይ ነው ማለቴ ከ እስከ የሚባል ስለሌለው ነው፤ ለዘለዓለም ስቃይ ስለሆነ ነው። ክረምት ብዬ መጥራቴ ስለዚሁ ነው፤ ኧረ እንደውም ከክረምት የባሰ ነው። እንዴት ያልከኝ እንደሆነ በዚሁ ክረምት ላይ የሚዘንበው ውኃ አይደለምና፤ እሳት እንጂ። በዚሁ ክረምት ዙርያህ ጨለማ የሚሆነው ከደመና ብዛት የተነሣ አይደለምና፤ ጽኑ ጨለማ እንጂ። የብርሃን ጭላንጭል የሌለው ጨለማ እንጂ። እዚህ የሚገቡት ሰዎች ተድላ መንግሥትን ማየት አይቻላቸውም፤ ሰማያትን ማየት አይቻላቸውም። ከመቃብር ውስጥ የባሰ ጨለማ ይውጣቸዋል እንጂ።

ወዳጄ ሆይ! አሁንስ አትርድምን? ወዴት እየሔድክ እንደሆነ አታስተውልምን? ፊትህንስ ወደ ልጁ መንግሥት አታደርግምን?"... አካሔድህን አስተካክል

"እያንዳንዱ ስለ ክርስቶስ የሚነገረው ነገር ቅድስት ቤተ ክርስቲያንን ከፍ ከፍ የሚያደርጋት ነው። ከክብሯ ሁሉ ከፍ ያለው ክብር ግን በመስቀሉ የተደረገው ድንቅ ነገር ነው። ሐዋርያው ይህን ቢያውቅ "ከጌታችን ከኢየሱስ ክርስቶስ መስቀል በቀር ሌላ ትምክሕት ከእኔ ይራቅ" አለ ገላ.6፡14።

ሲወለድ ጀምሮ ዕውር የነበረው ሰው በሰሊሆም ውኃ ታጥቦ እያየ መምጣቱ ድንቅ ነው። ሆኖም ዓለም ከታወረበት ዕውርነት አውጥቶ ብርሃን እንዲያይ ካደረገው ከመስቀሉ ጋር ሲነጻጸር ይህ ምንድነው? ከሞተ አራት ቀን የሆነው በመቃብርም ያደረው አልዓዛር እንደገና መነሣቱ ታላቅ ነገር ነው። ሆኖም በኃጢአት የሞተውን ዓለም ነፍስ ዘርቶ እንዲነሣ ካደረገው ከመስቀሉ ኃይል ጋር ሲነጻጸር ይህ ምንድነው? አምስቱ እንጀራዎች አምስት ሺሕ አባዎራዎችን ማጥገባቸው ድንቅ ነው። ሆኖም ዓለም ሁሉ ነግሦበት ከነበረው ረኀብ በዕውቀት ብርሃን እንዲጠግቡ ካደረገው ከክርስቶስ ኃይል ጋር ሲነጻጸር ይህ ምንድነው? ሰይጣን ለዓመታት ሲያሰቃያት የነበረችው ሴት ከእስራት መፈታትዋ ታላቅ ነገር ነው። ሆኖም ሁላችንን በኃጢአታችን ምክንያት ተጠላልፈን እንድንታሰር የሆንበትን የኃጢአት ሰንሰለት ከበጣጠሰው ኃይል ጋር ሲነጻጸር ምንድነው?

ዓለም ስለዳነ የምታደንቁ አትሁኑ! ይልቁን የሞተው ዕሩቅ ብእሲ ሳይሆን የእግዚአብሔር አብ የባሕርይ ልጅ በመሆኑ ይህንን አድንቁ እንጂ።"

❖ ቅዱስ ቄርሎስ ዘኢየሩሳሌም

+++ ***<u>ከሶርያዊው ጋር በገበታ ላይ</u>*** +++

.... በጣም በተራብክበት ዕለት ነው እንበል። ከፊትህ ምግብ ቀርቦልህ አንተም ለመብላት ጓጉተህ እያለ አንድ አባት ማዕዱን ለመባረክ ተነሡ። አባ የመዓድ ጸሎታቸውን ትንሽ ረዘም ቢያደርጉት ምን ይሰማሃል?

መቼም በተራበ አንጀትህ በአፍህ አሜን እያልክ በልብህ መራገምህ አይቀርም። "እኔ ጸሎቱን መች ጠላሁ ነገር ግን 'ሰሎሞን ለሁሉም ጊዜ አለው' ብሎ የለ?" እያልህ ከራስህ ጋር ትሟገት ይሆን? መቼም ጸሎቱ አብቅቶ የኦርቶዶክስ ቤተ ክርስቲያን ከጌታ በተማረችው ሥርዓት (ሉቃ 24:30) ካህኑ ከእንጀራው ቆርሰው ሲሠጡህም ንዴትህ ላይበርድ ይችላል። ማዕዱ ሲጀመር ግን ቂምህ ረስተህ ደስ ብሎህ ትመገባለህ። ሶርያዊው ያለውን ብትሰማ ግን ራስህን ትታዘበዋለህ።

ሶርያዊው ቅዱስ ኤፍሬም ከመብላት በፊት ለሚደረገው ጸሎት እጅግ ትልቅ ቦታ ከሚሠጡ አባቶች አንዱ ነበር። እርግጥ ነው በመጽሐፈ መነኮሳት ምግብ አቅርቦ ሊባርክ ጸሎት ከጀመረ በኋላ ምግቡን ረስቶ በተመሥጦ ጸሎት ሲያደርግ ያደረና ሰዓቱ አልፎ የቀጣዩ ቀን ጾም የገባበት አባት ታሪክም አለ። በእርግጥ የእግዚአብሔር ስም ምግብ ለሆናቸው አባቶች ከሰማያዊው ማዕድ ገበታ ተነሥተው ወደ ምድራዊው ምግብ መምጣት ቁልቁለት ይሆንባቸዋል። እኛ ሥጋዊያኑ ደግሞ በሰማያዊው የጸሎት ገበታ ላይ ቀርበን እንኳን ስለ ምድራዊው ምግብ ማሰብ አናቆምም።

በእርግጥ ለመብላት ፈጣሪን ማመስገን ለምን ያስፈልጋል?

ቅዱስ ኤፍሬም ስለ ምግብ ጸሎት በደረሰው መጽሐፉ (Table Blessings of Mar Ephrem) ላይ "አዳም በገነት እያለ ዕፀ በለስን ከመብላቱ በፊት አላመሰገነም ፣ መብላቱም አመጽ ሆኖ ተቆጠረበት ፣ (አዳምን ለማዳን ለካሣ የመጣው) ጌታ ግን ማዕድን አመስግኖና ባርኮ ይቆርስ ነበር" በማለት ይናገራል። እስቲ አዳምና ሔዋን ዕፀ በለስን የበሉበት ዕለት እናስታውስ።

"ሴቲቱም ዛፉ ለመብላት ያማረ እንደ ሆነ፥ ለዓይንም እንደሚያስጎመጅ፥ ለጥበብም መልካም እንደ ሆነ አየች፤ ከፍሬውም ወሰደችና በላች፤ ለባልዋም ደግሞ ሰጠችው እርሱም ከእርስዋ ጋር በላ።" (ዘፍ 3:6)

"ወሰደችና በላች" "ሰጠችውና በላ" የሚሉት ቃላት አዳምና ሔዋን ሳያመሰግኑ መብላታቸውን ፍንትው አድርጎ ያሳያል። ምናልባትም ከመብላታቸው በፊት በጸሎት አመስግነውት ቢሆኑ ኖሮ የፈጣሪያቸውን ትእዛዝና ያደረገላቸውን ሁሉ አስበው ከኃጢአት ሊከለከሉ ይችሉም ነበር።

ቅዱስ ኤፍሬም ሰው በመብላቱ ካላመሰገነ ከእንስሳት አይለይም ይላል። እንስሳት ስለሚበሉት ነገር አመስግነው አያውቁም። (አንድ አባት ዶሮ ውኃ ስትጠጣ ቀና የምትለውን ለምስጋና ይሆን? ሲሉ ሰምቼ ነበር /ውኃውን ማውረዱ እንዳለ ሆኖ ነው/) ስለዚህ ቅዱስ ኤፍሬም "በልተው ጠጥተው እንደማያመሰግኑ እንደ እንስሳት አንሁን" ይላል።

አክሎም በገበታ ላይ ቁጭ እንዳልን እየበላንም እናመስግን እያመሰገንን እንብላ "የሚያስመርረን ረሃብ ከተወገደልን ፣ ጥማችን ከተቆረጠልን አሁን ያለ መታወክ እናመስግን" ይለናል። ለማመስገናችን ምክንያቱ በእያንዳንዱ ምግብ ውስጥ የፈጣሪ ሥራ ስላለ ነው። ይህ ድንቅ አባት በውብ የዝማሬ ግጥሞቹ ዘርዝሮ ይናገራል።

እንጀራ ወይም ዳቦ ስትበላ ይህ እንጀራ ከአፈር መገኘቱን አስታውሰህ ታውቃለህ? ታዲያ የፈጣሪን ሥራ ማድነቅ የለብህም? ጣፋጭ ጭማቂ ስትጠጣስ ይህ ጭማቂ ከእንጨት ላይ የተገኘ መሆኑን አስተውለሃል? ለምግቡ ጣዕም የሠጠው ከእሾሃማ እንጨት የተጨመቀ ዘይት እንደሆነ ለምን ትረሳለህ? ከዚህ በላይ ምን አስደናቂ ቸርነት አለ? ጨው ባይኖር ይህ ምግብ ውኃ ውኃ ይል አልነበረም? ጨውን እንደ ድንጋይ ከሚረገጥበት ሥፍራ ያስቀመጠልህን ፈጣሪ ሳታመሰግን እንዴት ትበላለህ? ይላል ቅዱሱ።

ቅዱስ ኤፍሬም እውነት አለው። ምግብ ያበሰሉልንን ባለሙያ ሰዎች እናመሰግናለን ፣ እናሞግሳለን። ምግብን የፈጠረውን እንዴት ዘነጋነው? የምግቡ ጣዕም አስደነቀን የምግቡን ፈጣሪ ግን ለማመስገን ጥቂት ደቂቃዎች እንኳን እንዴት መታገሥ ተሳነን?

ጣፋጭ ምግብ ያበሰሉልልን ሰዎች "እጅሽ ይባረክ!" ብለን እናመሰግናለን። የአብሳዮቹን እጅ ከሚበስለው ነገር ጋር የፈጠረውን ጌታ ግን አናስታውሰውም። ምግብ ቤት ገብተን ለጥቂት ሰዓት ተመላልሰው ቦታ ሠጥተው ጥሩ ምግብና መጠጥ ከአክብሮት ጋር ላቀረቡልን አስተናጋጆች ምስጋና እናቀርባለን ፣ ዝናቸውን ለሌላም ሰው እንነግራለን።

እንደ ክቡር እንግዳ ሁሉን በምድር ላይ አሰናድቶ ሲጨርስ የፈጠረንንና ከተፈጠርንበት ዘመን እስካሁን ድረስ በዝናም አብቅሎ በፀሐይ አብስሎ የሚመግበን ፈጣሪ ግን ለማመስገን ጊዜ ማጣታችን ምንኛ ያሳዝናል?

ቅዱስ ኤፍሬም ምግብ ላይ ቁጭ ብላችሁ ስለ እሳትም አመስግኑ ይላል :-

"እሳት አይበላም ፣ በእርሱ ለሚበስሉ ምግቦች ሁሉ ግን ጣዕምን ይሠጣቸዋል። በምግቡ ጣዕም ውስጥ የእሳቱ ትኩስነት አለ ፣ ነበልባሉ ግን የለም። ሙቀቱ ግን በእጃችን ላይ ነው ማቃጠሉ ግን ከእኛ ርቋል" ስለዚህ እሳትን ድንቅ አድርጎ የፈጠረን አምላክ እያደነቃችሁ ብሉ ይላል።

"ጌታችን እንጀራና ዓሣን አበርክቶ ባበላ ጊዜ እንደተመገቡት ሰዎች እንሁን እነርሱ ሲበሉ የተመገቡት በሥጋቸው ብቻ ሳይሆን በነፍሳቸውም ነበር። አፋቸው ዓሣና እንጀራውን ከመብላት አላረፈም ፣ ጎሊናቸው ደግሞ ፈጣሪን ከማድነቅ አላረፈም። ይልቁንም ከምግቡ

በላይ ምግቡን ለሠጣቸው ጌታ ማወቃቸው በልጠባቸው ምስጋናቸው ከመመገባቸው አይሎ ነበር።" (ዮሐ 6:13)

ቅዱስ ኤፍሬም አላቆመም ፣ እየበላችሁም ስለ እግዚአብሔር ተነጋገሩ ፣ "ገበታችሁ የመንግሥተ ሰማያት ገበታ ይሁን" ይላል። ገበታ ላይ ስለ ምን እናውራ? ካልን ደግሞ ብትፈልጉ ስለ ገበታ አውሩ ይለናል።

አብርሃም ቤት እግዚአብሔር ተገኝቶ ስለቀረበለት ገበታ ተነጋገሩ። (ዘፍ 19:1) ደጃውን አልዓዛር ከደጁ አስተኝቶ ሲበላ ስለነበረው ስለ ባለጸጋ ገበታ ተነጋገሩ (ሉቃ 16:21) ስትበሉ "ብራብ አብልታችሁኛል" ስትጠጡም "ብጠማ አጠጥታችሁኛል" የሚለውን ቃል አስታውሱ።

በገበታችሁ ላይ ወይን ቀርቦ ከሆነም ብዙ ነገር ያጨዋውታል። ወይን ሳይጠጡ ስለኖሩት የኢዮናዳብ ልጆች ተነጋገሩ (ኤር 35) ወይኑን ስትቀዱ ጳውሎስ ለጢሞቴዎስ "ስለ ሆድህ ትንሽ የወይን ጠጅ ጠጣ" እንዳለው ተወያዩ። (1ጢሞ 5:23) በዚያውም ወይን ጠጅ ማብዛት ሎጥንና ኖኅን ለምን ዓይነት ጥፋት እንደዳረጋቸው እያነሣችሁ ከመስከር ተቆጠቡ። (ዘፍ 9:21 ፣ 19:33)

በገበታ ላይ ሰው ከማማት ቃሉን መወያየት ይሻላል ባይ ነው። ማር ኤፍሬም እንዲህ ይላል:

"አንዳንድ ሰው ሊበላና ሊጠጣ ተቀምጦ የሚያኝከውን ሥጋው አያጣጥመውም። ሳኦል ሥጋ ለመመገብ ተቀምጦ የዳዊትን ሥጋ ይበላ ነበር። በገሃድ ወይን እየጠጣ በስውር ግን የዳዊትን ደም ይጠጣ ነበር።" (1 ሳሙ 20:24)

የዮሴፍ ወንድሞችም ሊበሉ ተቀምጠው ወንድማቸውን ለመግደል ከጉድጓድ ጥለውት ይማከሩ ነበር። ምግቡን ከነገር ጋር እየተጎራረሱ ሲበሉ ደስ አላቸው። ዮሴፍ "ስትሰግዱልኝ አየሁ" ብሎ ሕልሙን ከነገራቸው ቀን ጀምሮ እንደዚያች ቀን ምግብ ጣፍጧቸው የበሉት ምግብ አልነበረም።

የዋሁ ዮሴፍ በግብፅ ገዥ ሆኖ ከተሾመ በኋላ ግን እየበሉ የሸጡትን ወንድሞቹን በቤተ መንግሥት እንዲበሉ ወደ ገበታው ጠራቸው። "ከወንድሞቹ ጋር እስከበላበት ቀን ድረስ ዮሴፍ የግብፅ እንጀራ አልጣፈጠውም ነበር። ከወንድሞቹ ጋር እስከጠጣበት ቀን ድረስ የፈርኦን ወይን አላስደሰተውም ነበር።"

"ችግር ለራሳችን እንድንጸልይ ያነቃቃናል፤ ፍቅር ደግሞ ለሌሎች ሰዎች እንድንጸልይ ያስገድደናል።"

❖ **ቅዱስ ዮሐንስ አፈወርቅ**

"ስስታም መኾን አንድ ነገር ነው፤ ባለጸጋ መኾን ደግሞ ሌላ ነገር ነው። ስስታም ሰው ባለጸጋ አይደለምና፤ ብዙ ነገሮችን በእጁ ለማስገባት የሚፈልግ ነው፤ ብዙ ነገሮችን ስለሚፈልግም መቼም

መች ባለጸጋ መኾን አይችልም። ስስታም ሰው የሀብት አዛዥ ሳይኾን ዘበኛ ነው፤ ጌታ ሳይኾን ባርያ ነው። ስስታም ሰው ካስቀመጠው ወርቅ ይልቅ ከሥጋው ቆርሶ ቢሰጥ ይመርጣል።"

- ቅዱስ ዮሐንስ አፈወርቅ

---

† □ የመንፈስ ቅዱስ ጸጋ

መንፈስ ቅዱስ በሐዋርያት ላይ ወረደ ሲባል አንዳንዶቹ የመንፈስ ቅዱሰ አካሉ የወረደባቸው ይመስላቸዋል ይህ ግን የተሳሳተ አመለካከት ነው ። በመንፈስ ቅዱስ አካል እና ስጦታ መካከል ያለው ልዩነት ጠንቅቆ ማወቅ ከስህተት ላይ ከመውደቅ ያድነናል ።

የመንፈስ ቅዱስ አካሉ ሳይሆን የሚሰጠው ጸጋው ነው ። መጽሐፍ ቅዱስ የመንፈስ ቅዱስ ጸጋ በተለያየ አገላለጥ ይገልጸዋል ። አንድ ጊዜ መንፈስ ቅዱስ ሌላ ጊዜ መንፈስ እያለ ይጠራዋል ። ለአብነት ያህል ብንጠቅስ ዩሐ 3*34 " እግዚአብሔር መንፈሱን ሰፍሮ አይሰጥምና " መንፈሱን ሰፍሮ አይሰጥም ሲል የእግዚአብሔር መንፈስ እንደማይሰፈር ጸጋውም ልክ ወሰን የሌለው መሆኑን መግለጽ ነው ።

- የሐዋ 19*2 "መንፈስ ቅዱስ ተቀበላችሁን ? አላቸው የመንፈስ ቅዱስ አካል ማለቱ ሳይሆን ጸጋውን ማለቱ ነው ። ሐዋ 10*49 ቃሉን በሰሙት ሁሉ ላይ መንፈስ ቅዱስ ወረደ አሁንም አካሉ ማለት አይደለም ስጦታውን ለማለት ነው ። የዚህ አባባል ትርጉም በዚህ ምዕራፍ ቁጥር 45 ላይ እንዲህ ሲል ይገልጸዋል ... በአህዛብ ላይ የመንፈስ ቅዱስ ሥጦታ ስለፈሰሰ ተገረሙ ይላል ።

እንግዲህ ከላይ እንደተገለጸው ሁሉ መጽሐፍ ቅዱስ የመንፈስ ቅዱስ ስጦታ አንድ ጊዜ መንፈስ ሌላ ጊዜ መንፈስ ቅዱስ እያለ ይጠራዋል ። እንዲህ ካልሆነ ግን ማለትም የመንፈስ ቅዱስ አካሉ ነው የሚሰጠው የሚወርደው ከተባለ የእግዚአብሔርን ምሉዕነት ስፍሀነት አለማወቅ መሆኑን ያሳያል ። እንዲሁም እግዚአብሔር ፍጡር ይመስል መውጣት መውረድ የለበትም ።

የመንፈስ ቅዱስ ጸጋ ኢሣያስ እንዲህ ሲል ይዘረዝረዋል የእግዚአብሔር መንፈስ የጥበብና የማስተዋል መንፈስ የምክር የኃይል መንፈስ የእውቀትና እግዚአብሔርን የመፍራት መንፈስ ... ኢሳ ፲፩*፲፪

የጸጋ ስጦታ ልዩ ልዩ ነው መንፈስ ግን አንድ ነው ። [አካሉ አንድ ሲሆን ስጦታው የበዛ ነው ማለቱ ነው] የጥበብ ቃል የሚሰጠው አለ ፤የእውቀት ቃል የሚሰጠው አለ ድውይ የመፈወስ ሥልጣን የሚሰጠው አለ ወዘተ በዚህ ሁሉ ሁሉንም የሚረዳው መንፈስ ቅዱስ አንድ ነው ። [፩ቆሮ ፲፪*፬-፲፪]

"ስስታም መኾን አንድ ነገር ነው፤ ባለጸጋ መኾን ደግሞ ሌላ ነገር ነው። ስስታም ሰው ባለጸጋ አይደለም፤ ብዙ ነገሮችን በእጁ ለማስገባት የሚፈልግ ነው፤ ብዙ ነገሮችን ስለሚፈልግም መቼም መች ባለጸጋ መኾን አይችልም። ስስታም ሰው የሀብት አዛዥ ሳይኾን ዘበኛ ነው፤ ጌታ ሳይኾን ባርያ ነው። ስስታም ሰው ካስቀመጠው ወርቅ ይልቅ ከሥጋው ቆርሶ ቢሰጥ ይመርጣል።"

- **ቅዱስ ዮሐንስ አፈወርቅ**

<u>ቤተ ክርስቲያን Vs ሆስፒታል</u>

(በቅዱስ ዮሐንስ አፈወርቅ)

እግዚአብሔር የሚወዳችሁ አንድም እግዚአብሔርን የምትወዱት ልጆቼ! ተጠራርታችሁ ወደ አባታችሁ ቤት ለመምጣት ያደረጋችሁትን ቅንአት ተመልክቼ ደስ ተሰኝቼባችኋለሁ። እኔም ይህን ቅንአታችሁን አይቼ ስለ ነፍሳችሁ ጤና ይበልጥ እንዳስብ አድርጎኛል። ቤተ ክርስቲያን ቀዶ ጥገና የሚደረግባት ሐኪም ቤት ናት። የሥጋ ቀዶ ጥገና ግን አይደለም፤ የነፍስ ቀዶ ጥገና ነው እንጂ። የምናክመው የሥጋን ቁስል አይደለም፤ መንፈሳዊ ቁስልን እንጂ። መድኃኒቱም ቃለ እግዚአብሔር ነው። ይህ መድኃኒት በምድር ላይ ከሚበቅሉት ዕፅዋት የተቀመመ አይደለም፤ ከሰማያት ከሚመጣው ቃል እንጂ። ይህን መድኃኒት በቁስል ላይ ለመጨመር ሐኪሞች አያስፈልጉም፤ የሰባክያነ ወንጌል አንደበት እንጂ። ቀዶ ጥገናውን ለማከናወን ብዙ ሰዓታትን አይፈጅም። ቀዶ ጥገናው ላይሳካ ይችላል ተብሎ የሚጠረጠር አይደለም። ከጊዜ በኋላ ወይም በሌላ ሕመም ምክንያት የተደረገው ቀዶ ጥገና ሊከሽፍ ይችላል ተብሎም አይገመትም። ሐኪሞች የሚሰጡን መድኃኒት እንዲህ ዓይነት ችግር ሊያጋጥመው ይችላል። ሐኪሞች የሚሰጡን መድኃኒተ ሥጋ ለጊዜው ብርቱ ነው፤ ሰውነታችን እያረጀ እንደሚሔደው ኹሉ መድኃኒቱም በጊዜ ሒደት ብርታቱን እያጣ ይሔዳል። ሌላ ደዌ ዘሥጋ ሲገጥመንም መቋቋም የሚችል አይደለም። ምክንያቱም መድኃኒቱን የቀመሙት ሰዎች ስለኾኑ። ከእግዚአብሔር የሚሰጠን መድኃኒት ግን እንደዚህ አይደለም። ምንም ያህል ጊዜ ቢቆይም አይበላሽም፤ ጊዜው አያልፍበትም፤ ኃይሉም ብርታቱም ያው ነው አይቀንስም።

ሙሴ የተቀበለው ቃለ እግዚአብሔር በጊዜው የነበሩትን ሰዎች ፈውሷቸዋል፤ አሁንም ያ ቃል ይፈውሳል። የመፈወስ ኃይሉ ብርታቱ እስከ አሁን ድረስ አላጣም፤ ሌላ ምንም ዓይነት በሽታም አላሸነፈውም። ይህን መድኃኒት ለመግዛት ብር አይበቃውም፤ ቅን ልቡና ብቻ ነው የሚያስፈልገው። በዚህ መድኃኒት ባለጸጋውም ድኻውም እኩል ይታከማሉ። ወደ ምድራዊው ሆስፒታል ሲኼድ ባለጸጋው ብር ስላለው ያሻውን ሕክምና አግኝቶ ወደ ቤቱ ይመለሳል፤ ድኻው ግን ብር ስለሌለው መድኃኒቱንም መግዛት ስለማይችል ሳይታከም ከነሕመሙ ወደ ቤቱ ይመለሳል። ይህ ከቤተ ክርስቲያን የሚሰጠው መድኃኒት ግን በብር የሚገዛ አይደለም። ይህን መድኃኒት ለማግኘት የሚያስፈልገውም ብር ሳይኾን እምነትና ምግባር ነው። እምነትና ምግባር የከፈለ ሰው ይህን መድኃኒት ማግኘት ይቻላል። እነዚህን የከፈለ ጤናውን አግኝቶ ወደ ቤቱ ይመለሳል። በመኾኑም ድኻውም ባለጸጋውም እኩል ታክመውበት ይሔዳሉ።

እንደዉም ከባለጸጋው ይልቅ ድኻው በመድኃኒቱ ይበልጥ ተጠቅሞ ይሔዳል። ለዚህስ ምክንያቱ ምንድነው? ምክንያቱም ባለጸጋው ብር ስላለው በብዙ ሐሳብ የተያዘ ነው። ሀብታም ነኝ ብሎ ስለሚያስብ ትዕቢተኛ ነው። ሕይወቱን የሚመራው በቸልተኝነት ነው። በስንፍና ስለሚያዝ መድኃኒት የኾነውን ቃሉን ለማድመጥ ስልቹ ነው። ድኻው ግን በቅንጠትና በስንፍና ኑሮ ስለማይኖር፣ ጊዜውን በእንተ ፈንቶ ነገሮች ስለማያሳልፍ መድኃኒቱ ነፍሱን ለማግኘት ንቁ ነው። ቃሉን ለማድመጥ ፈጣን ነው። ቸልተኝነት አይጠጋውም። የተባለውን ለማድመጥ ልቡናው ዘወትር ዝግጁ ነው። የሚከፍለው ክፍያ ብዙ ነው ማለት ነው፤ የሚያገኘውም መድኃኒት እንደዚያ ብዙ ነው።

ይህን ኹሉ ዘርዝሬ መናገሬ ግን ባለጸጋውን ኹሉ በደፈናው መኰነኔ አይደለም። ድኻውንም ኹሉ እንደሁ ማመስገኔ አይደለም። ምክንያቱም ሀብት በራሱ መጥፎ አይደለም፤ መጥፎ የሚያደርገው የእኛ አጠቃቀም ነው። ድኽነቱም በራሱ በጎ አይደለም፤ በጎ የሚያደርገው የኛ አጠቃቀም ነው። ባለጸጋው ነዌ ወደ ሲያል የተወረወረው ሀብታም ስለነበረ አይደለም፤ ጨካኝና ሰብአዊነት የማይሰማው ክፉ ስለነበረ ነው እንጂ። አልዓዛርም በአብርሃም ዕቅፍ የተቀመተው እንዲሁ ድኻ ስለነበረ አይደለም፤ ድኻም ቢኾን አመስጋኝ ስለነበረ እንጂ።

ይህን በማስተዋል ታደምጡ ዘንድ እማልዳችኋለኁ። አንዳንድ መልካም የኾነ ነገር አለ። አንዳንድ መጥፎ የኾነ ነገርም አለ። አንዳንዱ ደግሞ መጥፎም በጎም ኀን ያለው አለ። ሀብትና ድኽነት ግን በጎም ክፉም አይደሉም። ኹለቱም በጎ ወይም ክፉ የሚኾኑት እንደተጠቃሚው ሰው ነው። ሀብታችሁ ለበጎ አድራጎት የምትጠቀሙበት ከኾነ በጎ ነው። ከዚሁ በተቃራኒ ለክፉ ግብር የምታውሉት ከኾነ ግን ክፉ ነው። ክፉ ነው ማለቴ ግን ሀብቱ በራሱ ክፉ ኾኖ አይደለም፤ ክፉ ያደረገው የእናንተው አጠቃቀም ነው። ድኽነቱም ቢኾን እግዚአብሔርን ለማመስገን የምትጠቀሙበት ከኾነ ሹመት ሽልማታችሁ ብዙ ነው። በድኽነታችሁ አመካኝታችሁ እግዚአብሔርን የምታማርሩ ከኾነ ግን ድኽነታችሁ ክፉ ነው። ነገር ግን ሀብታችሁ በራሱ በጎ ወይም ክፉ እንዳልኾነ ኹሉ ድኽነታችሁም በራሱ ክፉ ወይም በጎ ኾኖ አይደለም። በጎ ወይም ክፉ የሚያደርገው የእናንተው አያያዝ ነው። እግዚአብሔርን ማመስገን ወይም ማማረር የሚመነጨው ከድኽነቱ ሳይኾን ከእኛ ነው። ሀብት መልካም ነው፤ መልካም የሚኾነው ግን ኃጢአት ላልሠራበት ሰው ብቻ ነው። ድኽነትም መጥፎ ነው፤ መጥፎ የሚኾነው ግን እምነት ለሌለው ሰው ነው። እምነት የሌለው ሰው አይጠግብም፤ ዘወትር እግዚአብሔርን ያማርራል፤ ዘወትር ብስጩ ነው፤ "እግዚአብሔር ስለምን ፈጠረኝ?" እያለ ይበሳጫልና ድኽነት እምነት ለሌለው ሰው መጥፎ ነው።

ስለዚህ ባለጸጎችን እንዲሁ በደፈናው አንውቀሳቸው፤ ድኽነትንም እንዲሁ አንጥላው። መውቀስ ካለብን እነዚህን ኹለቱንም በአግባቡ የማይጠቀሙባቸው ሰዎችን ነው። አስቀድሜ እንደተናገርኩት ድኽነት ወይም ሀብት በራሳቸው መጥፎ ወይም በጎ አይደሉምና። ስለዚህ በቤተክርስቲያን የሚሰጠው መድኃኒት ድኻውም ባለጸጋውም እኩል ታክመውበት ይሔዳሉ። ከባለጸጋው ይበልጥ ደግሞ ድኻው። የቃለ እግዚአብሔር ጥቅሙ መድኃኒተ ነፍስ መኾኑ ብቻ አይደለም፤ ጥራቱ በጊዜ ብዛትም አይበላሽም። በሌላ በሽታ ተጨማሪ ጉዳትን አያመጣም።

በነጻ የሚታደል ነው። የድኻውም የባለ ጸጋውም ዓቅም ያገናዘበ ነው። ከዚህ ባልተናነሰ መልኩ ሌላም ጥቅምም አለው። እርሱስ ምንድነው? አንድ ታካሚ ለቀዶ ጥገና ወደዚህ በመጣ ጊዜ ቁስሉ ሌላ ሰው እንዲያየው አይደረግም። ከቤተ ክርስቲያን ውጪ ወደኾነው ሆስፒታል ብትሔዱ ግን አንድ የቀዶ ጥገና ልዩ ባለ ሙያ (Specialist) አስቀድሞ የታካሚውን ቁስል ሳያይ የቁስል ፋሻን ማድረግ አይችልም።

በቤተ ክርስቲያን ዘንድ ግን እንዲህ አይደለም። አንደኛ በአንድ ጊዜ ብዙ ሕመማን ይታያሉ። ኹለተኛ ሕክምናው የሚሰጠው በምሥጢር ነው። የእያንዳንዱን ኃጢአተኛ ኃጢአትን በአደባባይ አንናገርም። ከዚያ ይልቅ መጀመሪያ ኹሉንም አንድ ላይ እናስተምራለን። ከዚያም እያንዳንዱ ሰው ሕሊናውን እንዲያደምጥ እናደርጋለን። ከዚያም እያንዳንዱ ሰው ካስተማርነው ትምህርት እንደ በሽታው ዓይነት የሚስማማውን መድኃኒት እያነሣ ይወስዳል። ሰባኬ ወንጌሉ የቤተ ክርስቲያኒቱን ዶግማንና ቀኖናን ያስተምራል። በዚያም አብሮ ክፉ ምግባርን ይገሥፃል፤ በጎ ምግባርን ያወድሳል። ዋልጌነትን ይነቅፋል፤ ንጽህናን ከፍ ከፍ ያደርጋል። ትዕቢትን ይገሥጻል፤ ትሕትናን ያመሰግናል። መድኃኒተ ሥጋ በውስጡ ሕመሙን ማከም የሚችሉ ብዙ ንጥረ ነገርን እንደያዘ ኹሉ ከሰባኪው የሚወጣው ቃለ እግዚአብሔርም እንደዚሁ ለእያንዳንዱ ሰው የሚኾን ፈውስን ይዟል። ቃሉ ኹሉም እየሰማ ይነገራል፤ ወደ እያንዳንዱ ሕሊና እንዲገባ ይደረጋል። በምሥጢርም ሕክምናውን ያከናውናል። የታማሚው ቁስል ሳይገለጥ በስውር ጤናውን ይመልስለታል።

ታዲያ መድኒተ ሥጋን ለማግኘት የምንፋጠነውን ያህል ቃለ እግዚአብሔርን ለመማር፥ ተምረንም ከመስማት ባለፈ (አጋንንትም ይሰማሉና) በተግባር መድኃኒትነቱን ተጠቅመንበታልን?

□ሁላችንም የቻልነውን በመቋጠር እንለወጥ

□ያለፈ ነገር አይቀዪርም ፣ ላወቀበት ሰው ግን ያለፈው ለወደፊቱ የራሱ የሆነ ትምህርት አለው ፣ ካለፈው ነገርህ ተማር እንጅ በፍፁም አታማርር ፣ ማማረር ነገህን በጎ አያደርገውም የሰዎች ሃሳብ የአንተን ማንነትአይገልፅም ፣ማንነትህ አንተ ውስጥ ነው ያለው ፣ መልካም አድርግ ሌላውን እርሳው የሁሉም ሰው የህይወት መንገድ (ጉዞ) ይለያያል ፣ ጊዜው በደረሰ ሰው ሁኔታ አትቅና ለሁሉም ጊዜ አለው ።

□መኪና ገዛ ብለህ "እኔስ" አትበል ጊዜህ ሲደርስ መኪናዎች ወይም 'ፕሌን' ትገዛለህ ፣ ያውም ለመኖር አስፈላጊ ከሆነ ፣ ደግሞም እንዴት እንደገዛው የት ታውቃለህና ? ተወው በራስህ ላይ አተኩር ፣ ያለህ ነገር በቂ ነው ። በሰዎች ደስታ ደስ ይበልህ ፣ ክፉ አትመኝ ፣ በሃዘናቸውም አብረህ እዘን ሲያዝኑ አትደሰት ፣ ሰው ከሆንክ የሰው ነገር ይሰማህ ፣ይህ ማለት ግን ተንኮል

እየሠሩ ከሚደሰቱ ሰዎች ተደሰት ማለት አይደለም ። ሰው እያስከፋ ብሎም እየገደለ የሚደሰት አለ ፣ አንተ ከተጎዳው ሰው ጋ ሁን ፣ አስተውል ።

□ጊዜ የማይፈውሰውና የማይቀይረው ነገር የለም አንተም ጊዜው ይቀይርህ ዘንድ ፍቀድለት ፣ በተሰጠህ ጊዜ ለመልካም ነገር ሱሰኛ ሁን ። የስራ ጉዳይ ውስጥህ የሚችለውና የሚያምንበት ተሰጥኦ ምን አለህ ? ምን አይነት ስራ መስራት ትችላለህ ? አስተውል ጓደኛህን አትመልከት ፣ ትለያያላችሁ ፤ አለማችን በትምህርት ብቻ ወይም በጥበባት ብቻ ወይም በተወሰኑ ዘርፎች አይደለችም እየኖረች ያለችው ፣ በጣም ብዙ ነገሮች ናቸው እየደገፏት ያቆሟት ፤ አንተም ጥቂትም ብትሆንያለህን ችሎታ አውጣው ፣ ቁፋሮ ነው ወይስ ቾክ ይዞ ማስተማር ነው ወይስ መምከር መገሰፅ ምንድነው? ቆንጆ ሽሮ ወጥ እየሰሩ መሸጥ ነው ፣ የድንጋይ ቅርፅ (ኮብልስቶን) እየሰሩ መኖር ነው ፣ ምንድነው ??? እባክህ ፈልገው አጎልብተው ጀምረው ፣ "ምን ይሻለኛል ?" እያልክ ጊዜህ እንዳያልቅ ፣

በእርግጥ ጊዜህ ሳይሆን አንተ ነህ የምታልቀው ።

□ጊዜ የማይፈውሰውና የማይቀይረው ነገር የለም አንተም ጊዜው ይቀይርህ ዘንድ ፍቀድለት ፣ በተሰጠህ ጊዜ ለመልካም ነገር ሱሰኛ ሁን ። የስራ ጉዳይ ውስጥህ የሚችለውና የሚያምንበት ተሰጥኦ ምን አለህ ? ምን አይነት

ስራ መስራት ትችላለህ ? አስተውል ጓደኛህን አትመልከት ፣ ትለያያላችሁ ፤ አለማችን በትምህርት ብቻ ወይም በጥበባት ብቻ ወይም በተወሰኑ ዘርፎች አይደለችም እየኖረች ያለችው ፣ በጣም ብዙ ነገሮች ናቸው እየደገፏት ያቆሟት ፤ አንተም ጥቂትም ብትሆን

ያለህን ችሎታ አውጣው ፣ ቁፋሮ ነው ወይስ ቾክ ይዞ ማስተማር ነው ወይስ መምከር መገሰፅ ምንድነው? ቆንጆ ሽሮ ወጥ እየሰሩ መሸጥ ነው ፣ የድንጋይ ቅርፅ (ኮብልስቶን) እየሰሩ መኖር ነው ፣ ምንድነው ??? እባክህ ፈልገው አጎልብተው ጀምረው ፣ "ምን ይሻለኛል ?" እያልክ ጊዜህ እንዳያልቅ ፣

በእርግጥ ጊዜህ ሳይሆን አንተ ነህ የምታልቀው ።

<u>ደብረ ምጥማቅ (ግንቦት 21)</u>

ከእመቤታችን 33ቱ በዓላት አንዱ ነው፤ በዚህ ቀን ግብጽ ደብረ ምጥማቅ በተባለ ቦታ በተሰራች ቤተክርስቲያን እመቤታችን ጻድቃንን መላእክትን አስከትላ ትገለጽላቸው ነበር፤ እስላምም ክርስቲያንም በግልጽ ይመለከቷት ነበር። ከየአገሩ ያሉ ሰዎች ይሰበሰባሉ ድንኳን ተክለው ሰቀላ ሰርተው አጎበር ጥለው ይከትማሉ፤ ድንግልም ከግንቦት 21 ቀን ጀምሮ ለአምስት ተከታታይ ቀናት ሳታቋርጥ ትገለጽላቸው ነበር፤ ህዝቡ የተለያየ ጥያቄ

ይጠይቃታል አዳም አባታችንን አሳይን ይሏታል ገሚሱ ነብዩ ዳዊትን ገሚሱ ቅዱስ ጊዮርጊስን አሳይን ይሏታል አንዳንዱም ከዚህ ቀደም የሞተ ዘመዱን እንድታሳየው ይጠይቃታል፤ እርሷም ለሁሉም ፍቃዳቸውን ትፈጽምላቸው ነበር፤ አዳምን ስትጠራው ከሔዋን ጋር ዳዊትን ስትጠራው ከበገናው ጋር ቅዱስ ጊዮርጊስን ስትጠራው ከጸአዳ ፈረሱ ጋር ነው። ወይ ግሩም ታዲያ ይህ በዚያ ደጉ ዘመን ነበር፤ አሁን ግን ኃጢያታችን ሲበዛ በረድኤት ካልሆነ በገሃድስ ተገልጻ አትታይም ለበቁ ካልሆነ።

- ከእመቤታችን ረድዔት በረከት ይክፈለን

የሰኔ ዖም

አንዳንዶች የሰኔ ዖም የቄስ ዖም ነው በሚል ከመዖም ወደኋላ ሲሉ ይታያሉ ነገር ግን ቅድስት ቤተክርስቲያን በአዋጅ ከምትዖማቸው ሰባት አፅዋማት አንዱ እንደመሆኑ መጠን እያንዳንዱ ክርስቲያን ቢዖመው እጅግ በርካታ በረከቶችን ያገኝበታል ከነዚህም ጥቂቶችን እነሆ

1.**በረከተ ሐዋርያት ይገኝበታል**:- ይህን ዖም መጀመርያ ዖመው እንድንዖመው ሰርዐት የሰሩልን ሐዋርያት ናቸዉ ስለዚህም ዖሙ መታሰቢያነቱ የሐዋርያት ነው የጻድቅ መታሰቢያ ደግሞ ለበረከት ነው ። ምሳ.10፥7 እኛም የሰኔን ዖም ብንዖም የሐዋርያቱን በረከት እናገኛለን ሐዋ.13፥1-3 ሐዋ.14፥23

2. **በስራችንና በአገልግሎታችን በረከት እናገኛለን**:- ሐዋርያት ይህን ዖም የዖሙት አገልግሎታቸው እንዲከናወንላቸው እንዲባረክላቸው ነው ነብዩ ነህምያም እየሩሳሌምን የመስራት ተግባሩ እንዲባረክለት በዖመው ዖም ስራው ሁሉ ተባርኮለታል። ነህም.1፥4። እኛም የሰኔን ዖም ብንዖም በዕለት ተዕለት ተግባራችን በረከት እናገኛለን።

3. **ዝናብ ምህረትን ጠለ በረከትን እናገኛለን**:- የሰኔ ዖም በአገራችን የክረምቱ መግቢያ ላይ የሚዖም ዖም ነው ይህም መጪው የክረምቱ ወራት የተስተካከለ የምህረት ዝናም እንዲኖረው ያደርጋል በነብዩ ኢዩኤል ዘመን ዝናብ ጠፍቶ ዛፎቹ ሳይቀር በደረቁ ጊዜ በዖም በፀሎት ወደ እግዚአብሔር በተማፀኑ ሰዓት ዝናመ በረከትን አግኝተዋል። ኢዩ.1፥13-14

4. **በረከተ ምርትን እናገኛለን**:- የሰኔ ዖም በሃገራችን ገበሬው ዘር መዝራት በሚጀምርበት ጊዜ የሚዖም ዖም ነው ሰለዚህም በዚህ ሰዓት የሚዖመው ዖም ዘርን እንዲባረክ በረከት እንዲበዛ ያደርጋል ይህም አገር ወገን ከረሃብ ከችግር ነፃ እንዲወጣ ያደርጋል በነብዩ ኢዩኤል እንደተገለጸው በዖም የዕህል የመጠጥ በረከት ይገኛል ። ኢዩ.2፥12-14

5. **የነፍስ በረከትን እናገኛለን**:- ዖም በመንፈስ የደከመች የዛለች ነፍስን ያበረታል የነፍስን ቁስል ይፈውሳል ስጋዊ ኃይልን ያደክማል የሥጋን ፈቃድ ለነፍስ ያስገዛል መዝ.108፥24 ፤ ገላ.5፥24 የዓለምን ሃሳብ ያስወግዳል ከእግዚአብሔር ያስታርቃል ማቴ. 17፥21 ሚስጥር ይገልጣል ዘስ.34፥27-28 ፤ ዳን. 10፥1-3 "በአምላካችን ፊት እራሳችንን እናዋርድ ዘንድ

ከርሱም የቀናውን መንገድ ለእኛና ለልጆቻችን ለንብረታችንም ሁሉ እንለምን ዘንድ ..... ያምን አውጃለሁ " መጽሐፈ ዕዝራ.8፥21

ከመዋዕለ ያሙ ረድኤት በረከት ያሳትፈን !

ያሙን የኃጢአት መደምሰሻ የዲያብሎስ ድል መንሻ የመንግሥተ ሰማያት መውረሻ ያድርግልን አሜንንንን !!!

❖ ***<u>ብሂለ አበው</u>***

□ "መሬት ሁን ከመባል ያነሰ የውርደት ቋንቋ የለም ሰው አምላክ ሆነ ከመባል በላይ የሚበልጥ የክብር ቋንቋ የለም"። **ቅዱስ ዮሐንስ አፈወርቅ**

□ "ከመጠኑ በላይ የሚመሰገንና የሚከበር ሰው ብዙ ኩነኔ ያገኘዋል ከሰው ዘንድ ከቁም ነገር መልካም ሰርቶ ያለፈ ሰው ግን በሰማይ ታላቅ ክብር ይጠብቀዋል"። **አባ አውር**

□ "በኃይል አብዝቶ መመገብ ሳይቆጠርከወጣትነት ጋር የኃጢአት ሐሳብን በግድ እንዲመጣ ያደርጋሉ"። **ማር ይስሐቅ**

□ "ከሰዎች መካከል አንዱ እንደ ከንቱ እና ምንም እንደሌለህ እንደ አላዋቂ አድርጎ ቢቆጥርህ ከአፈር እንደተፈጠርህና ወደ እርሱም እንደምትመለስ ተናገር አንተ ወራዳ ከንቱ ብሎ ቢሰድብህም አንተ ራስህን አፈርና አመድ ነኝ ብለህ ጥራ እራሱን እንዲህ ብሎ ከጠራው ከተከበረው አባት ከአባታችን አብርሃም የበለጥህ አይደለህምና"። **ቅዱስ ባስልዮስ ዘቂሳርያ**

□ "ቤተ ክርስቲያን በጥምቀት አማካይነት አንድ የሆኑ ክርስቲያኖች የትንሳኤያቸውና የድኅነታቸው ምንጭ የክርስቶስ አካል ናት"። **ቅዱስ ዮሐንስ አፈወርቅ**

□ "ከሰው ወንድሙን የሚመክር ሰው እነሆ የፍቅሩን ጽናት ብዛት ያስረዳል፤ ባልንጀሮች ፊት የሚነቅፈው ግን የቅናቱን ጽናት ያስረዳል የምቀኝነቱን ጽናት ተለይቶያስረዳል"። **ማር ይስሐቅ**

□ "የመጠመቂያውን ውኃ ተራ ውኃ አድርገህ አትመልከተው፤ በውኃው አማካኝነት የሚሰጠውን ፀጋ እንጂ"። **ቅዱስ ቄርሎስ**

□ "ቂመኛ ከመሆን ተከልከል፤ ቂመኛ ሰው ሥጋ የለበሰ ሰይጣን ነውና"። **አረጋዊ መንፈሳዊ**

□ "ቤተ ክርስቲያን መጠጊያችን ዘኢየሩሳሌምነች፤ ቤተ ክርስቲያን የኖህ መርከብ ነች፤ በውስጧ እንጠለላለን፤ ከውጪዋ ግን ማዕበልና ቀላያት ተከፍተዋል"። **ቅዱስ እንድርያስ**

□ "የንጉሡ የክብር ዘቦች በፊት ለፊት በተጠንቀቅ ሲቆሙ ወደ ግራም ወደ ቀኝም አይመለከቱም ቅዱስእንደዚሁ አንድ ሰው በእግዚአብሔር ፊት ሲቆም ሁል ጊዜ በፍርሃት ሆኖ እርሱን ይገባል"። **አባ ሰራጵዮን**

□ "ቅዱሳን ለመለኮታዊ ማዕጠንት የተቀጣጠሉ ዕጣን ሲሆኑ የተቀጣጠሉትም ሊመለከትበፈጣሪያቸው ፍቅር ነው"። **ማር ይስሐቅ**

□ "ሰው አገሩን ጥሎ በሔደ ጊዜ ሁሉ ያዝንለታል፤ ከርስቱ ከጉልቱ በተለየ ጊዜ ሁሉ ይራራለታል ያለቅሱለታል፤ ከመንግስተ ሰማያት ከተድላ፤ ከመዓዛ የተለየ ሰውማ ምን ያህል ለቅሶ ማልቀስ ምን ያህል ዕምባ ያፈስ ዘንድ የሚገባው ምን ያህል ይሆን"። **ቅዱስ ዮሐንስ አፈወርቅ**

+ታዛዥነትና ተዘክሮተ እግዚአብሔር+

አባ ዮሐንስ ኃጢር ከሚታወቅባቸው መልካም ምግባራት መካከል የሚጠቀሱለት ናቸው ታዛዥነትና ተዘክሮተ እግዚአብሔር። አንደ ቀን አባ ባሞይ ዮሐንስ ኃጢርን የደረቀ እንጨት ተክሎ ለምልማ እስክታፈራ ድረስ ውኃ እንዲያጠጣት አዘዘው። ያለማንገራገር በትጎትና ሆኖ አሥራ ሁለት ምዕራፍ ያህል ከሚርቅ ቦታ በቀን ሁለት ጊዜ ውኃ እያመላለሰ ያጠጣ ጀመር። በሦስተኛው ዓመት ያቺ በትር ለምልማና አብባ ያማረ ፍሬ አፈራች። አባ ባሞይ በዮሐንስ ታዛዥነት እጅግ ተደሰተ። ፍሬውን ለቅሞ ለገዳሙ መነኮሳት እንካችሁ ይህ የታዛዥነት ፍሬ ነው እያለ ሰጣቸው። መነኮሳቱም ይህን ተአምር ባዩ ጊዜ አደነቁ። ለቅን እና ታዛዥ ሰው ይህን ጸጋ የሰጠ እግዚአብሔርንም አመሰገኑ።

"መልካም ሰው ከእግዚአብሔር ዘንድ ሞገስ ያገኛል።" ምሳሌ 12፤2

"ልጆቼ ፦ እግዚአብሄርን በእምነት በፀሎት እንሻው ከእኛ የጠፋ ገንዘባችንን ነቅተን ተግተን በብዙ ድካም እንድንሻው እንዲሁ ሃሳባችንን ወደእግዚአብሄር ልናቀርብ ይገባናል፤ ልጃችን ቢጠፋብን ፈልገን በቅርብ ያላገኘነው እንደሆነ ሃይላችንን በድካም ድካማችንን በሃይል የምንለውጥ አይደለንምን? የጠፋውን ልጃችንን ስለመፈለግስ እናገኘው ዘንድ የብሱን በእግር ባህሩን በመርከብ የምንዞር አይደለንምን? ፈልገንም ያገኘነው እንደሆነ ዳግመኛ እንዳይጠፋብን ለመጠበቅ እንተጋ የለምን?

እንዲህ ከሆነ መሓሪ እግዚአብሄርን በእምነትና በፀሎት እንሻው ዘንድ ምን ያህል ይገባን ይሆን? እግዚአብሄርን ፈልጉት ነጋዴ ወርቅ ቢጠፋበት ወርቁን ያገኘው እንደሆነ ሁሉን ቦታ እንደሚፈልግ እንዲሁ እግዚአብሄርን ፈልጉት እናት ልጇ ቢጠፋባት እስክታገኘው ድረስ አርፋ እንደማትቀመጥ እንዲሁ እግዚአብሄርን ፈልጉት እግዚአብሄርን እሹት ፈልጉት እስክታገኙት ድረስ በእምነት በፀሎት እሹት።"

- **ቅዱስ ዮሐንስ አፈወርቅ**

"በጽድቁ ከሚመካ ጻድቅ ሰው ይልቅ ስለ ኃጢአቱ የሚያለቅስ ዘማዊን እግዚአብሔር ይወደዋል።"

- **አባ ጊዮርጊስ ዘጋስጫ**

"አማርያም በእንተዝ ናፈቅረኪ ወነአብየኪ ፤ ማርያም ሆይ ስለዚህ እንወድሻለን ከፍከፍ እናደርግሻለን"

- **ቅዳሴ ማርያም**

"መልካም ያደረጉ ብዙ ሴቶች አሉ አንቺ ግን ከሁሉ ትበልጫለሽ።" ምሳ. 31፡29

ክርስቶስን ያከበሩ፤ መንገዱን የተከተሉ ብዙ ሴቶች አሉ፤ እውነትን የመሰከሩ፤ ስለ ቃሉ የኖሩ ብዙ ሴቶች አሉ፤ መስዋዕትነትን የከፈሉ በሰማዕትነት ያለፉ ብዙ ሴቶች አሉ፤ ታላላቅ የምድር ነገስታትን፤ ታላላቅ ነቢያትን የወለዱ ብዙ ሴቶች አሉ፤ ከነዚህ ሁሉ ግን አንቺ ትበልጫለሽ።

ቅድስት ድንግል ሆይ አንቺ እኮ፡- ሰማይ ዙፋኑ ምድር መረገጫው የሆነ፤ ድንቅ መካር ኃያል አምላክ የሰላም አለቃ፤ ሁሉ በእርሱ የሆነ ከሆነውም አንዳችም እንኳን ያለርሱ ያልሆነ፤ ዓለምን ሁሉ ከሞት ወደ ሕይወት የመለሰ፤ መንበሩን የሚሸከሙ ኪሩቤልና ሱራፌል የሚንቀጠቀጡለት፤ የሁሉ ፈጣሪ፤ የሁሉ አምላክ እናት ነሽ። በፊትም አሁንም ወደፊትም ካንቺ በቀር ፈጣሪዋን ልጄ ብላ የምትጠራ ሴት አልነበረችም፤ የለችም፤ አትኖርምም ክርስቶስም እናቴ ብሎ የሚጠራት ብቸኛዋ ሴት አንቺ ነሽ በእውነት ከሁሉ ትበልጫለሽ።

እናት ስትሆኝ ድንግል፤ ድንግል ስትሆኝ እናት በእውነት ከሁሉ ትበልጫለሽ። ትውልድ ሁሉ ብጽዕት ብሎ የሚጠራሽ ብቸኛዋ ሴት በእውነት ከሁሉ ትበልጫለሽ። እግዚአብሔር መርጦና ጠብቆ ያስቀረሽ ዘር በእውነት ከሁሉ ትበልጫለሽ። ለዓለም ሁሉ ድህነት ምልክት የሆንሽ በእውነት ከሁሉ ትበልጫለሽ።

እናቴ ሆይ እንግዲህ እኔ ምን ልናገር? ሺህ ቃላትን ብደረድር ያንቺን ክብር ልገልፀውስ እንደምን እችላለው? አዎ አሁንም እላለሁ "መልካም ያደረጉ ብዙ ሴቶች አሉ አንቺ ግን ከሁሉ ትበልጫለሽ።" ምሳ. 31፡29

የቅድስት ድንግል ማርያም በረከቷ በሁላችን ላይ ይደር፤ ምልጃ ቃል ኪዳኗ ይጠብቀን። አሜን!!!

"ልጆቼ ፦ እግዚአብሄርን በእምነት በፀሎት እንሻው ከእኛ የጠፋ ገንዘባችንን ነቅተን ተግተን በብዙ ድካም እንድንሻው እንዲሁ ሃሳባችንን ወደእግዚአብሄር ልናቀርብ ይገባናል፤ ልጃችን ቢጠፋብን ፈልገን በቅርብ ያላገኘነው እንደሆነ ሃይላችንን በድካም ድካማችንን በሃይል የምንለውጥ አይደለንምን? የጠፋውን ልጃችንን ስለመፈለግስ እናገኘው ዘንድ የብሱን በእግር ባህሩን በመርከብ የምንዞር አይደለንምን? ፈልገንም ያገኘነው እንደሆነ ዳግመኛ እንዳይጠፋብን ለመጠበቅ እንተጋ የለምን?

እንዲህ ከሆነ መሓሪ እግዚአብሄርን በእምነትና በፀሎት እንሻው ዘንድ ምን ያህል ይገባን ይሆን? እግዚአብሄርን ፈልጉት ነጋዴ ወርቅ ቢጠፋበት ወርቁን ያገኘው እንደሆነ ሁሉን ቦታ እንደሚፈልግ እንዲሁ እግዚአብሄርን ፈልጉት እናት ልጇ ቢጠፋባት እስክታገኘው ድረስ አርፋ እንደማትቀመጥ እንዲሁ እግዚአብሄርን ፈልጉት እግዚአብሄርን እሹት ፈልጉት እስክታገኙት ድረስ በእምነት በፀሎት እሹት።"

- ቅዱስ ዮሐንስ አፈወርቅ

(ወደ ሮሜ ሰዎች ምዕ. 8)

14፤ በእግዚአብሔር መንፈስ የሚመሩ ሁሉ እነዚህ የእግዚአብሔር ልጆች ናቸውና።

15፤ አባ አባት ብለን የምንጮኽበትን የልጅነት መንፈስ ተቀበላችሁ እንጂ እንደገና ለፍርሃት የባርነትን መንፈስ አልተቀበላችሁምና።

16፤ የእግዚአብሔር ልጆች መሆናችንን ያ መንፈስ ራሱ ከመንፈሳችን ጋር ይመሰክራል።

17፤ ልጆች ከሆንን ወራሾች ደግሞ ነን፤ ማለት የእግዚአብሔር ወራሾች ነን፥ አብረንም ደግሞ እንድንከበር አብረን መከራ ብንቀበል ከክርስቶስ ጋር አብረን ወራሾች ነን።

.

35፤ ከክርስቶስ ፍቅር ማን ይለየናል? መከራ፥ ወይስ ጭንቀት፥ ወይስ ስደት፥ ወይስ ራብ፥ ወይስ ራቁትነት፥ ወይስ ፍርሃት፥ ወይስ ሰይፍ ነውን?

36፤ ስለ አንተ ቀኑን ሁሉ እንገደላለን፥ እንደሚታረዱ በጎች ተቆጠርን ተብሎ እንደ ተጻፈ ነው።

37፤ በዚህ ሁሉ ግን በወደደን በእርሱ ከአሸናፊዎች እንበልጣለን።

38፤ ሞት ቢሆን፥ ሕይወትም ቢሆን፥ መላእክትም ቢሆኑ፥ ግዛትም ቢሆን፥ ያለውም ቢሆን፥ የሚመጣውም ቢሆን፥ ኃይላትም ቢሆኑ፥

39፤ ከፍታም ቢሆን፥ ዝቅታም ቢሆን፥ ልዩ ፍጥረትም ቢሆን በክርስቶስ ኢየሱስ በጌታችን ካለ ከእግዚአብሔር ፍቅር ሊለየን እንዳይችል ተረድቼአለሁ።

ሰላም ለሁላችሁ፦ ጌታ ኢየሱስ ክርስቶስ በምድር ላይ ፍቅር የሚያሲዝ ተወዳጅና በጭካኔ የተጠላም ነው። አንድ የጥንት ጸሐፊ እንዳለው በምድር ላይ ባሉ የሐይማኖት ቡድኖች ሽኩቻ ምክንያት በብዛት የሚጠሉት በስም ክርስቲያን የሆኑ ህዝቦች ናቸው። ለምን እንደሚጠሉትም ምክንያት የላቸውም። ብዙዎቹም እንደማይወዱት እንኳ አያውቁም። ይህ ስልታዊ የዲያብሎስ ውጊያ ነው። አንዳንድ ባልና ሚስቶች በአንድ ቤት እያሉ አልጋ ለይተው ሳይፋቱ ተፋተው እንደሚሩ ሁሉ ብዙዎችም ከጌታቸው ጋ እንዲሁ ይኖራሉ። በሚወዱትም ዘንድ የተለየ ነው። ሴት ወስዳ ሊጥ ውስጥ እንደሸሸገችው እርሾ ነው። የወደዱትን ሰዎች ህይወት ያጣፍጠዋል። ውስጣቸው ታልቅ ሃይል ያድራል። እንደ ወይን ያሰክራል። ካንተ ወዴት እንሂዳለን አንተ የህይወት ውሃ አለህ ያሰኛል። ዓለምን የማስካድ ሃይል አለው። ክፉን የመታገስ ጉልበት ይሰጣል። ሃይለኛውን አንደበትና ክንድ አስሮ ይይዛል። ድንግል የወለደችው መሲህ ለብዙዎች ለመውደቅና ለመነሳት ምልክት ነው። የህይወትም አጀንዳ ነው። የቅራኔና የሰላም ምክንያት ነው። ምህረቱ እስከ ትወልድ ትውልድ ነው። የእስላሙም ፣ የቡዲውም፣ የሂንዱውም፣ የራሽናሉም፣የክርስቲያኑም ህዝብ መዳኛ ነው። ያለኦክስጂን መኖር እንደሌለ ያለእርሱ ምንም የዘለዓለም ህይወት የለም። ትውልዱን የሚያለመልም መስኖ ነው። ህጻናት የሚቀረጹበት የአብ መልክነው። ስሙ ቡሩክ ይሁን። የሚወዱት እልፍ አእላፋት ሆነው ይብዙ። (**ቀሲስ አሸናፊ ገ/ማርያም**)

"ጸሎት ለመጸለይ ስታስብ ረጅም ንግግር ማድረግ አስፈላጊ አይደለም:: እጅን ወደ ሰማይ ዘርግቶ እንዲህ ማለት ብቻ በቂ ነው "ጌታ ሆይ እንደ ፈቀድህና እንዳወቅህ ይቅር በለኝ":: ነገር ግን ፈተናው እየተጋጋለ ከመጣ እንዲህ በል "ጌታ ሆይ እርዳኝ" እግዚአብሔር ምን እንደምንፈልግ ያውቀልና ምህረቱን ይገልፅልናል:: " (**አባ መቃርዮስ**)

<u>†□የመጽሐፍ ቅዱስ ጥናት:: †□</u>

□ዛሬ ቅዱስ ዮሐንስ አፈወርቅ ዮሐንስ ወንጌልን በተረጎመበት ድርሳኑ ስለ ቅዳሳት መጻሕፍት ንባብ የሰጠውን ምክር እናያለን::

✍□"የቅዱሳት መጻሕፍት ጥቅም እጅግ ብዙ እና ታላቅ ነው:: ከእነርሱም የሚመገኘው ጥቅም በቂ ነው:: ጳውሎስም ይህን ሲገልፅ እንዲህ አለ "በመጽናትና መጻሕፍት በሚሰጡት መጽናናት ተስፋ ይሆንልን ዘንድ አስቀድሞ የተጻፈው ሁሉ ለትምህርታችን ተጽፎአልና።" (ሮሜ15÷4:1ኛ ቆሮ 10÷11):: መለኮታዊ የሆኑት ቃላት የሁሉም አይነት መድኃኒት ግምጃ ቤት ነቸው:: ትዕቢትን ለማጥፋት ይሁን: የእንቅልፍን ፍላጎት ላማስታገስ(ስንፍናን ለማራቅ): የገንዘብን ፍቅር ከእግር በታች ለመርገጥ: በራስመተማመንን ለማነሳሳት: ትግስትን ለማግኘት ከመለኮታዊ ቃላት (ከቅዱሳት መጻሕፍት) አንድ ሰው የተትረፈረፈ ሀብትን ያገኛል:: (ቅዱስ ዮሐንስ አፈወርቅ የዮሐንስ ወንጌል ምዕራፍ 5 ትርጓሜ)

----ሰላም ለሁላችሁ ፦ እግዚአብሔር ሥራን በረከት አድርጎ ሰጠ። ሰው እንደ እርሱ ሰራተኛ እንዲሆን አስቦ ፈጠረው። ዛፎችን እንጂ ጠረጴዛ ና ወንበርን በጫካ ውስጥ አላኖረም። ወርቅንና የከበረ ማዕድንን በከርሰ ምድር ውስጥ ሰወረው። ውድ አልማዝ በብዙ ልፋት እንዲወጣ አርቆ አኖረው። እንጀራን በብዙ ሰልፍ መሃል አኖረው። ስሩና ብሉ እያለን እንደሆነ ተመልከቱ። ውጤትንና ስኬትን ከልፋት ጀርባ አቆመው። ከዚያም ባለፈ ተዓምር መስራት የሚችን አእምሮ ሰጠን። ግን ሁሉም ለምና ያልተነካ ነው። ሰው ነው የሚያዳብረው። አእምሮም ሥራም በሰው እጅ ነው ጉልበቱን የሚያወጣው። እኛና ሥራ ብንደመር ተዓምረኛ ዓለም ይፈጠራል። የሚያበራ ምድር ይኖረናል። ስለዚህም ለስራ ክብር ልሰጥ ይገባል። ያለመስራት ኃጢአት ነው። መልካም ያለማድረግ ነውና። ብሩክ ሁኑ።

ቀሲስ አሸናፊ ገ/ማርያም

□□መልእክት□□

(ወደ ኤፌሶን ሰዎች 1)

1፤ በእግዚአብሔር ፈቃድ የኢየሱስ ክርስቶስ ሐዋርያ የሆነ ጳውሎስ፥ በኤፌሶን ላሉት ቅዱሳን በክርስቶስ ኢየሱስም ላሉት ምእመናን፤

2፤ ከእግዚአብሔር ከአባታችን ከጌታም ከኢየሱስ ክርስቶስ ጸጋና ሰላም ለእናንተ ይሁን።

3፤ በክርስቶስ በሰማያዊ ስፍራ በመንፈሳዊ በረከት ሁሉ የባረከን የጌታችን የኢየሱስ ክርስቶስ አምላክና አባት ይባረክ።

4፤ ዓለም ሳይፈጠር፥ በፊቱ ቅዱሳንና ነውር የሌለን በፍቅር እንሆን ዘንድ በክርስቶስ መረጠን።

5፤ በበጎ ፈቃዱ እንደ ወደደ፥ በኢየሱስ ክርስቶስ ሥራ ለእርሱ ልጆች ልንሆን አስቀድሞ ወሰነን።

6፤ በውድ ልጁም እንዲያው የሰጠን የጸጋው ክብር ይመሰገን ዘንድ ይህን አደረገ።

7፤ በውድ ልጁም፥ እንደ ጸጋው ባለ ጠግነት መጠን፥ በደሙ የተደረገ ቤዛነታችንን አገኘን እርሱም የበደላችን ስርየት።

8፤ ጸጋውንም በጥበብና በአእምሮ ሁሉ አበዛልን።

9፤ በክርስቶስ ለማድረግ እንደ ወደደ እንደ አሳቡ፥ የፈቃዱን ምሥጢር አስታውቆናልና፤

10፤ በዘመን ፍጻሜ ይደረግ ዘንድ ያለው አሳቡም በሰማይና በምድር ያለውን ሁሉ በክርስቶስ ለመጠቅለል ነው።

11፤ እንደ ፈቃዱ ምክር ሁሉን የሚሠራ እንደ እርሱ አሳብ፥ አስቀድመን የተወሰንን በክርስቶስ ደግሞ ርስትን ተቀበልን።

12፤ ይኸውም፥ በክርስቶስ አስቀድመን ተስፋ ያደረግን እኛ ለክብሩ ምስጋና እንሆን ዘንድ ነው።

13፤ እናንተም ደግሞ የእውነትን ቃል፥ ይኸውም የመዳናችሁን ወንጌል፥ ሰምታችሁ ደግሞም በክርስቶስ አምናችሁ፥ በተስፋው መንፈስ በመንፈስ ቅዱስ ታተማችሁ፤

14፤ እርሱም የርስታችን መያዣ ነው፥ ለእግዚአብሔር ያለውን ሁሉ እስኪዋጅ ድረስ፥ ይህም ለክብሩ ምስጋና ይሆናል።

15፤ ስለዚህ እኔ ደግሞ በእናንተ ዘንድ ስለሚሆን በጌታ በኢየሱስ ስለ ማመንና ለቅዱሳን ሁሉ ስለሚሆን መውደድ ሰምቼ፥

16፤ ስለ እናንተ እያመሰገንሁ ስጸልይ ስለ እናንተ ማሳሰብን አልተውም፤

17፤ የክብር አባት የጌታችን የኢየሱስ ክርስቶስ አምላክ እርሱን በማወቅ የጥበብንና የመገለጥን መንፈስ እንዲሰጣችሁ እለምናለሁ።

18-19፤ ይህም የልባችሁ ዓይኖች ሲበሩ የመጥራቱ ተስፋ ምን እንዲሆን በቅዱሳንም ዘንድ ያለው የርስት ክብር ባለ ጠግነት ምን እንዲሆን ለምናምን ከሁሉ የሚበልጥ የኃይሉ ታላቅነት ምን እንዲሆን ታውቁ ዘንድ ነው፤

20-21፤ ክርስቶስንም ከሙታን ሲያስነሣው ከአለቅነትና ከሥልጣንም ከኃይልም ከጌትነትም ሁሉ በላይና በዚህ ዓለም ብቻ ሳይሆን ነገር ግን ሊመጣ ባለው ዓለም ደግሞ ከሚጠራው ስም ሁሉ በላይ በሰማያዊ ስፍራ በቀኙ ሲያስቀምጠው በክርስቶስ ባደረገው ሥራ የብርታቱ ጉልበት ይታያል፤

22፤ ሁሉንም ከእግሩ በታች አስገዛለት ከሁሉ በላይም ራስ እንዲሆን ለቤተ ክርስቲያን ሰጠው።

23፤ እርስዋም አካሉና ሁሉን በሁሉ የሚሞላ የእርሱ ሙላቱ ናት።

አንተም ኃጢያት ሰርተህ እግዚአብሔርን ካላሳዘንኸው በቀር ሽህ ጊዜ ወደ እቶን ብትጣልም እንኳን ምንም አይነካህምና ተስፋ አትቁረጥ ፣ እግዚአብሔርን አሳዝነህ እንደሆነ ግን በገነት ውስጥም ብትሆን ደኅንነት አይሰማህም። አዳምም በገነት ውስጥ ነበር ፣ ሆኖም እግዚአብሔርን ባሳዘነ ጊዜ ገነት ለእርሱ ምንም ጥቅምን አልሰጠችውም። እነዚህ ታዳጊዎችህ ደግሞ /ዳን. 3፣18/ በእቶን ውስጥ ነበሩ ነገር ግን አልበደሉም ነበርና እቶኑ በፍፁም አልጐዳቸውም። አዳም በገነት ውስጥ ነበር፣ ነገር ግን ግድየለሽ በመሆኑ ምክንያት ወድቋል በአንፃሩ ደግሞ ኢዮብ በአመድ ላይ ተቀምጦ ነበር ነገር ግን ሁል ጊዜ ንቁ ስለነበረ ድል አድርጓል ገነት ምን ያህል ከአመድ ይልቅ የተሻለ ቦታ ነው ነገር ግን አንድ ሰው እራሱን እስከ ጐዳ ድረስ የቦታው መልካም መሆን ነዋሪውን መልካም አያደርገውም ልክ እንደዚሁ የቦታው መጥፎነትም በሁሉም እረገድ እራሱን ለሚያበረታ ሰው አይጐዳውም። ስለዚህ እኛም በሁሉም እረገድ እራሳችንን እናበርታ፣ የሃብት ማጣትም ቢሆን ፣ ሞት እራሱም ቢሆን ሃይማኖታችንን ካልቀማን ከሰዎች

ሁሉ ይልቅ ደስተኞቹ እኛ ነን ጌታችን ክርስቶስም ይህንን በማስመልከት እንዲህ ብሎ አዝዞናል፦ " እንደ እባብ ልባሞች ሁኑ " /ማቴ.10፣16/። እባብ እራሱን /ጭንቅላቱን / ለማዳን ሲል ሌላው ሰውነቱን ለአደጋ እንደሚያጋልጥ ሁሉ አንተም እንዲህ አድርግ ። ሐይማኖትህን ለመጠበቅ ስትል ሃብትህን፣ ሰውነትህን ፣ የዚህ አለም ህይወትህን ወይም ያለህን ሁሉ እንኳን መስጠት ካለብህ ይህንን በማድረግህ በፍፁም አትዘን አንተ ሃይማኖትህን ይዘህ ወደ ወዲያኛው አለም ስትሄድ እግዚአብሔር ደሞ ሁሉንም ነገር እጅግ ውብ አድርጐ ይመልስልሃልና ከሃብት ከንብረት ይልቅም ከመግለፅ ሃይለ በላይ የሆኑ በጐ በጐ ነገሮችን ይሰጥሃልና።

(1ኛ ወደ ቆሮንቶስ ሰዎች ምዕ. 1)

11፤ ወንድሞቼ ሆይ፥ በመካከላችሁ ክርክር እንዳለ ስለ እናንተ የቀሎዔ ቤተ ሰዎች አስታውቀውኛልና።

12፤ ይህንም እላለሁ። እያንዳንዳችሁ። እኔ የጳውሎስ ነኝ፥ እኔስ የአጵሎስ ነኝ፥ እኔ ግን የኬፋ ነኝ፥ እኔስ የክርስቶስ ነኝ ትላላችሁ።

13፤ ክርስቶስ ተከፍሎአልን? ጳውሎስስ ስለ እናንተ ተሰቀለን? ወይስ በጳውሎስ ስም ተጠመቃችሁን?

የእለቱ ቃል □□ ትህትና

(የሉቃስ ወንጌል 18)

9፤ ጻድቃን እንደ ሆኑ በራሳቸው ለሚታመኑና ሌሎቹን ሁሉ በጣም ለሚንቁ ይህን ምሳሌ ነገራቸው፥

10፤ እንዲህ ሲል፦ ሁለት ሰዎች ሊጸልዩ ወደ መቅደስ ወጡ፥ አንዱ ፈሪሳዊ ሁለተኛውም ቀራጭ።

11፤ ፈሪሳዊም ቆሞ በልቡ ይህን ሲጸልይ፦ እግዚአብሔር ሆይ፥ እንደ ሌላ ሰው ሁሉ፥ ቀማኞችና ዓመፀኞች አመንዝሮችም፥ ወይም እንደዚህ ቀራጭ ስላልሆንሁ አመሰግንሃለሁ፤

12፤ በየሳምንቱ ሁለት ጊዜ እጦማለሁ፥ ከማገኘውም ሁሉ አሥራት አወጣለሁ አለ።

13፤ ቀራጩ ግን በሩቅ ቆሞ ዓይኖቹን ወደ ሰማይ ሊያነሣ እንኳ አልወደደም፥ ነገር ግን፦ አምላክ ሆይ፥ እኔን ኃጢአተኛውን ማረኝ እያለ ደረቱን ይደቃ ነበር።

14፤ እላችኋለሁ፥ ከዚያ ይልቅ ይህ ጻድቅ ሆኖ ወደ ቤቱ ተመለሰ፤ ራሱን ከፍ የሚያደርግ ሁሉ ይዋረዳልና፥ ራሱን ግን የሚያዋርድ ከፍ ይላል።

ተ ስለአባቶች አንደበት ስለ እርገት ተ

✍"ክርስቶስ ወደ ሰማይ ያረገው እራሱን (ስለራሱ) ለእግዚአብሔር አብ ለማቅረብ አይደለም:: እርሱ ሁል ጊዜ በአብ ዘንድ ነበረ: አሁንም አለ ለዘላለምም በወለደው (በአባቱ) እቅፍ ውስጥ ይኖራል:: ስለዚህ እኛን ወደ ነበርንበት ይመልሰን ዘንድ ቀድሞ እንደነበረው የአብን ፊት እንድናይ እርሱ እንደ ሰው ራሱን ወደ አብ ስለእኛ አቀረበ::" (የእስክንድርያው ቅዱስ ቄርሎስ)

" ወደ ልጁ ወደ ጌታችን ወደ ኢየሱስ ክርስቶስ ጎብረት የጠራችሁ እግዚአብሔር የታመነ ነው።"

(1ኛ ወደ ቆሮንቶስ ሰዎች 1:9)

"አንተ ልትበላው ያልፈለግኸው እንጀራ የተራቡት ሰዎች እንጀራ ነው። በቁም ሳጥንህ ውስጥ ሰቅለህ የተውከው ልብስ ዕርቃኑን የሆነው ሰው ልብስ ነው። የማታደርጋቸው ጫማዎችህ ባዶ እግሩን የሚሔድ ሰው ጫማዎች ናቸው። የቆለፍክበት ገንዘብ የደሃው ገንዘብ ነው። የማትፈጽማቸው የቸርነት ሥራዎች ሁሉ ኢፍትሐዊ ድርጊቶችህ ናቸው"

- ቅዱስ ባስልዮስ

ሰላም ለሁላችሁ፦ በእግዚአብሔር ቃልና በጸሎት የተቀደሰ ነው።1ጢሞ 4፥5 ልጆቹ ሆይ እጠገባችን ያለን የትኛውንም ጉዳይ በሁለቱ ጸጋዎች ሚዛን ልክ መጠበቅ ይኖርብናል። ተድላና ምኞት ከእግዚአብሔር ቃልና ከጸሎት ውጪ ወጥመድ ነው። ግን በሁለቱ ሲደገፍ ደስታ ነው። ችግርና ውጣውረድ ከጸሎትና ለቃሉ ድጋፍ ሲያጣ ህይወትን የሚያመሰቃቅል አውሎ ነፋስ ነው። በሁለቱ ሲደገፍ የጥበብና የስርዓት ትምህርት ቤት ነው። ወዳጅነት ያለ ሁለቱ ጸጋዎች ራስን መጥቀሚያ ብቻ ነው። በሁለቱ ሲደገፍ የማይወድቅ ፍቅር ነው። ስርዓት አክባሪነትና መንፈሳዊነት በሁለቱ ሲታገዝ መልካምነት ነው። ብቻውን ግን ግብዝነት ነው። ቃሉን ማስተማር በሁለቱ ጥላ ውስጥ መምራት ና ማሳረፍ ነው። ብቻውን ግን ሥራ ነው። ስለዚህ የሙሴን እጆች አሮንና ሆር እንደደገፉና ድል እንዳደረጉ በቃሉና በጸሎት የእኛም ክንድ ተደግፎ መቆም ይገባዋል።ዘጸ 17፥12

- ቀሲስ አሸናፊ ገ/ማርያም

ከእለታት አንድ ቀን አንድ አባት ወደ አባታችን አባ መቃርዮስ በኣት ሄደና "አባቴ ሆይ ድኅነትን አገኝ ዘንድ ምን ላድርግ?" ሲል ጥያቄ አቀረበላቸው። አባታችንም እንዲህ በማለት አሉት።

"ወደ መቃብር ሂድና ሙታንን ሰድበሃቸው ና" አሉት። ይህ አባትም የተባለውን አድርጎ ተመለሰ። አባታችንም "ምን አሉህ?" ሲሉ ጠየቁት። ሰውየዉም "ምንም አልመለሱልኝም" ሲል መለሰ። አባ መቃርዮስም "አሁን ደግሞ ሂድና ሙታንን አመስግናቸው" አሉት። ሄዶም አመሰገናቸው። "አሁንስ ምን አሉህ" ሲል በድጋሚ ጠየቁት። ሰውዬም "ምንም አልመለሱልኝም" ሲል መለሰ። አባታችን አባ መቃርዮስም: "ስትሰድባቸው ፤ስታመሰግናቸው እና ስታወድሳቸው ምንም አልመለሱም፤ አንተም ለነፍስህ ድህነትን ከፈለግህ እንደሞተ ሰው ሆነህ ኑር። ሰዎች ክፉ ቢያደርጉብህም፣ ቢያመሰግኑህም ምንም አይሰማህ" አሉት።

የምጽዋት ብዛት የሚመዘነው በሚሰ'ጠው ገንዘብ ቁጥር ሳይሆን ስጦታውን በሚሰጥ የልብ ስፋት ነው። አንዲት ድኻ ሴት ያላትን ጥቂት እንጀራ ምንም ከሌላት ከሌላ ሴት ጋር ተካፍላ የምትበላ ከሆነ፥ ወርቅን በሙዳዬ ምጽዋት ከሚጨምር ባለጸጋ ሰው እጅግ ትበልጣለች። ነገር ግን ምንም እንኳን ይህ እውነት እንደ ኾነ ብዙ ክርስቲያኖች ቢያውቁም፥ ምስጋና የሚሰጡት ወርቅ ለሰጠው ነው።

አንድ ባለጸጋ ጠቀም ያለ ገንዘብ ለቤተ ክርስቲያን ቢሰጥ እጅግ ያመሰግኑታል፤ ካለው የሀብት ብዛት የተነሣ ያንን በመስጠቱ ምንም ባይጎድልበትም እንኳ፥ በሰዎች ዘንድ እጅግ ቸር እንደ ኾነ ተደርጎ ይንቆለጳጳሳል። ድኻው ጥቂት ገንዘብ ቢሰጥ ግን ሰዎች ስለ እርሱ ምንም ትንፍሽ አይሉም። ምናልባት ያቺ የሰጣት ገንዘብኩ በኋላ እርስዋን በማጣቱ ምክንያት ተርቦ እንዲያድር ልታደርገው የምትችል ትኾን ይኾናል፤ ነገር ግን ይህን በማድረጉ የሚያመሰግነው አንድ ሰውስ እንኳ አይገኝም። በእውነት ያለ ሐሰት ምንም ሳይጎድልበት የሰጠውን ባለጸጋውን አመስግኖ ያለውን ኹሉ የሰጠውን ድኻ ሳያመሰግኑ ከሚቀሩ ከእነ ጭራሹ ምስጋና ባይኖር ይሻል ነበር።

ስለዚህ እውነተኛ ምጽዋት የሚባለው የባለጸጋውም ይኹን የድኻው በአግባቡና በሥርዓቱ ልናውቀው ይገባናል። ማመስገን የሚገባንም ከዚያ በኋላ ነው። በሌላ አነጋገር የምስጋናችን ስጦታም ሰዎች ከልባቸው ከሚሰጡት ገንዘብ ብዛት አንጻር ሊኾን ይገባል።

- ቅዱስ ዮሐንስ አፈወርቅ:

"ጻዲቁ ዮሴፍ እጅግ ከባድ የሆነ ውጪያዊ ውጊያ ከጲጥፋራ ሚስት ቢገጥመውም አልወደቀም ። እርሱ ኃጢአትን በልቡ ውስጥ ስላልተቀበለው ፈተናውንም አልተቀበለውም ። ስለሆነም ጥቃቱን ሊቋቋም ችሏል ። ዲያብሎስ አሳቦችን ያቀርብልሃል እንጅ ተቀብለህ ተግባራዊ እንድታደርጋቸው አያስገድድህም " ።

- አቡነ ሺኖዳ ሳልሳዊ

[የዲያብሎስ ውጊያዎች ፪ኛ መጽሐፍ]

"ሌቦች ባዶ ቤትን ለመበርበር አይመጡም፤ ወርቅና ብር ወዳለበት ቤት እንጂ። ዲያብሎስም ልክ እንደዚህ ነው፤ ሊፈትናቸው የሚመጣው መንፈሳዊ ሀብታትን ወዳከማቹት ነው።"

- (ቅዱስ ዮሐንስ አፈወርቅ)

"ጸምህና ምጽዋትህ ሁለት ዋጋ አላቸው። ከሰው ክብርን ሽተህ የምትጦም ከሆነ ኃጢአት በአንተ ላይ እንድትበረታ ደንቁርናህም እጅግ ጽኑ እንዲሆን እወቅ። ነገር ግን እጆችህን ለተቸገረ ሰው የምትዘረጋ ሕሊናህን ግን ወደ አምላክ የምታነሣ ከሆነ፣ እንዲሁም ስትጦም ጦምህን በእግዚአብሔር ፊት ያደረግህ እንደሆነ ከፈጣሪህ ዘንድ መልካምን ዋጋ ትቀበላለህ። ይህ ኃይለ ቃል "ለእናንተ በሰማይ መዝገብ ሰብስቡ መዝገብህ ባለበት ልብህ ደግሞ በዚያ ይሆናልና።"(ማቴ.6፡21) ብሎ ጌታችን ካስተማረው ትምህርት ጋር አንድ ዓይነት ትርጉም ያለው ነው።

ጦምና ምጽዋታችን በከንቱ ፈቃዳችን ምክንያት ለኃጢአት አሳልፎ እንዳይሰጠንና በደላችንንም እጥፍ ድርብ እንዳያደርግብን አምላካችን ይህን ማስተዋል ዘወትር ይሰጠን ዘንድ በዚህ የጦም ወር እንለምነው።

ለወደደንና በእኛ ጥቂት ድካም ዘለዓለማዊ ዋጋን ለሚሰጠን ለእርሱ ምስጋና ይሁን ዛሬም ዘወትርም ለዘለዓለሙ አሜን።

- (ቅዱስ ኤፍሬም)

"አንተ ሐሳብህን ልትመራዉ እንጂ፤ ሐሳብህ አንተን ሊመራ ቦታ አትስጠዉ፥ እዉነተኛ ክርስቲያን ስሜቱ የሚመራዉ ሳይሆን ስሜቱን የሚወመራ ነዉ።"

- ብጹዕ ወቅዱስ አቡነ ሺኖዳ ሳልሳዊ

ተ□ አንዳንድ ጊዜ የእግዚአብሔር ቃል በመከራ ውስጥ ይመጣል ።

አንድ ሰው መፍትሔ የሌለው የሚመስል መከራ ሊገጥመው ይችላል ። በዚህ ጊዜ የእግዚአብሔር ድምፅ መከራው የገጠመው ጥቂት ኃጢአቶችን ስለ ፈጸመ መሆኑን ከማስጠንቀቂያ ጋር ይነግረዋል ። አንዳንድ ጊዜ ደግሞ ቃሉ ንስሓ ከገባህ መከራው ፍጻሜ ያገኛል እያለ ውስጡን ሲመክረው ይሰማል ። ከዚህ በኋላ እግዚአብሔር ስለ ንስሓው ሲል ለሰውየው ይራራለታል ።

የእግዚአብሔር ድምፅ አንድ ሰው ሲታመም ወይም እርሱ የሚወደው ሌላ ሰው ሲታመም ሊመጣ ይችላል ። በዚህ ጊዜ እንዲጸልይ ወይም ስእለት እንዲሳል የሚመክረውን ድምፅ ከውስጡ ይሰማል ይህ ድምፅ የእግዚአብሔር ድምፅ ነው ።

የዮሴፍ ወድሞች እህል ሊገዙ ወደ ግብጽ ከወረዱ በኋላ በዚያ ችግር ሲገጥማቸው እርስ በእርሳቸው እንዲህ በማለት ተነጋግረው ነበር ፦ " በእውነት ወድማችንን በድለናል እኛን በማማጠን ነፍሱ ስትጨነቅ አይተን አልሰማነውና ። ስለዚህ ይህ መከራ መጣብን ።"/ ዘፍ 42*21/ ። ከዚህ በኋላ ለዮሴፍ እንዲህ ብለውታል ፦ " ለጌታዬ ምን እንመልሳለን ? ምንስ እንናገራለን ? ወይስ በምን እንነጻለን ? እግዚአብሔር የባሪያዎችህን ኃጢአት ገለጠ ..."/ዘፍ 44*16/ ኃጢአታቸውን እንዲያስታውሱ ጎላም እንዲገሰጹ ያደረጋቸው የእግዚአብሔር ድምፅ ነው ።

ነቢዩ ዳዊት የጌራ ልጅ በሆነው በሳሚ ሲሰደብ የእግዚአብሔር ድምፅ ውስጡን ስላለፈ ኃጢአቱ እየወቀሰው መሆኑን አዳምጧል ። ስለሆነም በዙሪያው ለነበሩ ሰዎች " "እግዚአብሔር ዳዊትን ስደበው ብሎታልና ይርገመኝ ። / 2ኛ ሳሙ 16*10/ በማለት በግልጽ ተናግሯል ።

ረሀብና የመሬት መንቀጥቀጥ በዓለም ሲደርስ የእግዚአብሔር ድምፅ በመላው ዓለም ውስጥ ይሰማል ። በዚህ ጊዜ የእግዚአብሔር ድምፅ የሚናገረን " ወደ እኔ ተመለሱ እኔም ወደ እናንተ እመለሳለሁ ።" / ሚል 3*7/ እያለ ነው ። ይህ ድምፅ በረሀቡ ወይም በመሬት መንቀጥቀጡ ጉዳት ለደረሰባቸው ሀገሮች የሚሆን የእርዳታ ጥሪ ለማሰማት ወይም ሌሎቹ ከእነርሱ ትምህርት በመውሰድ ንስሓ እንዲገቡ ለማድረግ ወይም ከእግዚአብሔር ጋር ለመገናኘት ዝግጅት እንዲያደርጉ ነው ።

ስለዚህ ማንኛውም ዓይነት መከራ ውስጥ ስትገቡ ከውስጣችሁ ያለውን የእግዚአብሔር ድምፅ አድምጡት እርሱ ለእናንተ ሊነግራችሁ የሚወደው ምን እንደ ሆነ ታውቃላችሁና ።

- ብጹዕነታቸው አቡነ ሺኖዳ ፫ኛ

"ልጆቼ! ከእሳተ ገሃነም እንዴት ልንተርፍ(ልንድን) እንደሚገባን እንጂ እሳተ ገሃነም የት እንዳለ ለማወቅ እጅግ የምንደክም አንኾን።"

- ቅዱስ ዮሐንስ አፈወርቅ

እኛ የኢትዮጵያ ኦርቶዶክስ ተዋሕዶ ቤተ ክርስቲያን አማኞች፡-

ኢየሱስ ስንል አምላክ አማልእክት፡ - የአማልክት አምላክ

ኢየሱስ ስንል እግዚእ ወአጋእዝት፡ - የጌቶች ጌታ

ኢየሱስ ስንል ንጉሠ ነገሥት፡ - የነገሥታት ንጉሥ

ኢየሱስ ስንል አልፋ ወ ኦሜጋ፡ - መጀመሪያው እና መጨረሻው፣ ፊተኛው ኋለኛው

ኢየሱስ ስንል ንጉሠ ሰማይ ወምድር፡ - የሰማይና የምድር ንጉሥ

ኢየሱስ ስንል ኤልሻዳይ፡- ኹሉን ቻይ

ኢየሱስ ስንል አዶናይ፡ - መድኃኔዓለም

ኢየሱስ ስንል ወልደ አብ ወልደ ማርያም፡ - የአብ ልጅ የማርያም ልጅ በተዋሕዶ ልደት የከበረ

ኢየሱስ ስንል ፈጣሬ ኩሉ፡ - ኹሉን የፈጠረ

ኢየሱስ ስንል እግዚአብሔር ማለታችን ነው።

ስሙን ስንጠራ ይኽ ሁሉ በልባችን ሰሌዳ ታስቦ ነው።

- **<u>ምክረ አበው</u>**

"ብቸኝነት የሚሰማን ከሰው ሳይሆን ከእግዚአብሔር ስንርቅ ነው"!!

☞«ሰው የለኝም፤» በማለት በተሚጠጠ ተስፋ ይህንን ቃል የተናገረው መጻጉዕ ነው።(ዮሐ 5፥7)

►"ወዳጄ " አንተም እንደ መፃጉዕ በዙርያህ ሰው አጥተህ ሰው የለኝም ብለህ ተስፋ ቆርጠህ ይሆናል ።

►የሚቀርብህ ሁሉ ያለህን ነገር ብቻ አይቶ እንደሚጠጋህ አውቀህ የልብ ወዳጅ በማጣትህ አዝነህ ይሆናል።

►ብትወድቅ ቀና የሚያረግህ ብትደናቀፍ ከልቡ እኔን የሚልህ የልብ ጓደኛ የለኝም ትል ይሆናል።

►ትናንትና በሰርግህ ላይ ነጭ ለብሰው ካንተ ጋር "ሲዘምሩ" የነበሩ ሰዎች ዛሬ በለቅሶክ ላይ ብን ብለው ጠፍተው ከሰው ተስፋ እንድትቆርጥ አድርገውክ ይሆናል ።

►ትናንት አጀቢ የበዛልህ ሰው ዛሬ ብቻህን ቆመህ ይሆናል ።

☞ወንድሜ በዚህ አትደነቅ ።

♦□ከክርስቶስ እጅ እንጀራና አሳ በበረከት ሲበሉ የነበሩ ሰዎች መች በ"መስቀሉ" ቀን ከእርሱ ጋር ቆሙ።

♦□ውሃው ወደ ወይን ጠጅ ሲቀየር በሰርጉ ላይ ነበሩ ፤ ደሙ ሲፈስ ግን በቀራኒዮ አልነበሩም ።

☞ታዲያ ህይወት ለሰጣቸውና ለሞተላቸው ምግበ ነፍስ ምግበ ስጋ ለሰጣቸው ለክርስቶስ ያልሆነ ሰው ላንተ ይሆናል ብለህ ታስባለህ ።በፍፁም አይሆንም !!

✿ሰው ሸንበቆ ነው ከተደገፍከው ይሰበራል ።

✿ተሰብሮም አይቀርም ይወጋሀል ።

☞ወንድሜ ያንተም ነገር ይሄ ነው !!

★ወዳጆችህ ቀን አይተው ቢከዱህ ፣

★ዘመዶችህ ማጣትህን አይተው ገሸሽቢያረጉህ ፣

★ብቻህን ከራስህ ጋር ብትቆም አትደነቅ።

☞ ግን በዚህ መካከል አንድ ነገር አስተዉል:-

✔□ጊዜን አይቶ የማይከዳ ፣

✔□በሁኔታዎች የማይለዋወጥ ፣

✔□ሁል ጊዜ ሰው ለሌላቸው ቀድሞ የሚደርስ ፣

✔□የጭንቅ ቀን ባለ ውለታ፣

✔□የቁርጥ ቀን ወዳጅ እግዚአብሔር ካንተ ጋር ነው።

☞ እርሱ ካንተ ጋር መሆኑን ካመንክ ሰው የለኝም እያልክ የምታንጎራጉረው መዝሙር ግጥሙም ዜማውም ይቀየራል !!!

♠□♠□<>♠□♠□<>♠□♠□<>♠□♠□<>♠□♠□<>♠□♠□

:

#ወዳጄ፥

☞ወደ ዋላ ተመለስና ታሪክ አጥና ፦

❶.ዮሴፍን ወንድሞቹ ሸጠውት ወደ ግብፅ ሲወርድ ሰው አልነበረውም፥ እግዚአብሔር ግን በጌታው በጲጥፋራ ቤት ከፍ ከፍ አደረገው።

❷.በጌታው ሚስት ተንኰል ወደ ወኅኒ ቤት በተወረወረ ጊዜም ሰው አልነበረውም፥ እግዚአብሔር ግን ከወኅኒ ቤት አውጥቶ በባዕድ ሀገር ገዥ አደረገው።(ዘፍ 39፥1-23፤ 41፥1-50።)

❸.ሙሴ በሕፃንነቱ ወንዝ ዳር ሲጣል ሰው አልነበረውም፥ እግዚአብሔር ግን ከተጣለበት አንሥቶ በፈርዖን ቤተ መንግሥት፥ የንጉሥ የልጅ ልጅ ተብሎ እንዲያድግ አደረገው። (ዘጸ 2፥1-10)

❹ ብላቴናው ዳዊት በኃያሉ በጎልያድ ፊት በቆመ ጊዜ ሰው አልነበረውም፥ ከወንጭፉ በስተቀር መሣሪያም አልነበረውም፥ እግዚአብሔር ግን ጎልያድን በአንዲት ጠጠር ግንባሩን ፈርክሶ ጣለለት።(1ኛሳሙ 17፥35-55።)

❺.ዳንኤልና ሠለስቱ ደቂቅ ተማርከው ወደ ባቢሎን

ሲወርዱሰው አልነበራቸውም፥ እግዚአብሔር ግን ጥበብን ሰጥቶ በባቢሎን ጠቢባን እና አውራጃዎች ላይ እንዲሾሙ አደረጋቸው።(ዳን 1 እና 2፤)

❻ በሰዎች ተንኰል፥ ሠለስቱ ደቂቅ ወደ ዕቶነ እሳት፥ ዳንኤል ደግሞ ወደ አናብስት ጉድጓድ በተጣሉም ጊዜ ሰው አልነበራቸውም፤ እግዚአብሔር ግን ቅዱስ ሚካኤልን እና ቅዱስ ገብርኤልን ልኮ አዳናቸው።(ዳን 3፥24፣6፥6)

❼.አልዓዛር በሞት ተይዞ፥ ተግንዞ፥ ወደ መቃብር በወረደ ጊዜ ሰው አልነበረውም፤ ጌታ ግን ከመቃብር አወጣው ።

(ዮሐ 11፥28-34)

:❽.ቅዱስ ጴጥሮስ በሰንሰለት ታስሮ ወደ ጨለማው ወኅኒ ቤት ሲወረወር ሰው አልነበረውም፥ ጌታ ግን መልአኩን ልኮ ከወኅኒ ቤት አወጣው።(የሐዋ 12፥1-11)

❾.ቅዱስ ጳውሎስና ሲላስ ወደ ወኅኒ ቤት ተወርውረው፥ ከግንድ ጋርም አጣብቀው ሲያስሯቸው ሰው አልነበራቸውም።

►በመንፈቀ ሌሊትም ይጸልዩ፥ እግዚአብሔርንም በዜማ ያመሰግኑ ነበር።

►ጌታም የእግር ብረቱን፥ የእጅ ሰንሰለቱን ፈትቶ፥ በሩንም ከፍቶ አውጥቶአቸዋል።(የሐዋ 16፥16-30።)

♠□♠□<>♠□♠□<>♠□♠□<>♠□♠□<>♠□♠□<>♠□♠□

☞ታዲያ ወዳጄ ይህ ላንተም ነው ።ይህ ህግ ዛሬም በህይወትህ ዉስጥ ይሰራል ። ብቻህን አይደለህም ።

♣□ዘመድ ላይኖርህ ይችላል ታማኝ ጓደኛ ላይወጣልህ ይችላል

♣□እናት ወይም የስጋ አባት ላይኖርህ ይችላል

♣□ግን ከሁሉ በላይ የሆነውን ወዳጅ ፣ ዘመድ ጓደኛ የሚተካ ፤ ከሁሉ በላይ ሆኖ ሁሉም በእርሱ ለእርሱ የሆነ ወዳጅ "አባት" አለህ!! በዚህ ኩራት ይሰማህ !!!

ሁለት ሰዎች በአንድ ጉዳይ አብረው ይጸልያሉ። አንደኛው ጸሎቱ ተመለሰለት፣ አንደኛው ሳይመለስለት ቀረ። በዚህ ጊዜ ጸሎቱ ያልተመለሰለት ምእመን፡- "ጌታ ሆይ ሁለታችንም እኩል ጸለይን ለእርሱ ሰጥተኸው ለእኔ የከለከልከኝ ለምንድን ነው?" አለው። እግዚአብሔርም፡- "ለእርሱ ባልሰጠው ይጠፋል፣ ላንተ ከሰጠሁህ ትጠፋለህ" አለው።

እግዚአብሔር ከራሳችን በላይ እኛን ያውቀናል። ለአንዳችን በመስጠት፣ አንዳችንን በመከልከል ዕድሜያችንን ያረዝመዋል። መስጠቱም መንሣቱም ሁለቱም ለፍቅር ነውና ስለሆነልን ስለሚሆንልንና ስላልሆነልን ነገር ሁሉ ተመስገን ማለትን አንርሳ።

እንደ ጋኔን ቅናተኛ የለም። ቅናቱ ግን በሰው ልጆች ላይ እንጂ እርሱን በሚመስሉ አጋንንት ላይ አይደለም። ሰው ግን በገዛ ወንድሙ ላይ ይቀናል፤ በአጋንንት እንኳን በጭራሽ የማይደረግ በገዛ ቤተ ሰቡ ላይ ይቀናል። ታዲያ እንደዚህ ዓይነት ሰው እንዴት ይቅርታን ያገኛል? እንዴት ምሕረት ቸርነትን ያገኛል?

+ ቅዱስ ዮሐንስ አፈወርቅ

ክፍል 1 ተፈፀመ